የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

# የተባበሩት መንግሥታት የንግድ እና ሰብአዊ መብቶች መመሪያ መርሖች

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶችን በሀገር ውስጥ ቋንቋዎች ለመተርጎም እና ለማሰራጨት በአዋጅ ቁጥር 210/1992 አንቀጽ 6 (8) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን የተባበሩት መንግሥታት የንግድ እና ሰብአዊ መብቶች መመሪያ መርሖች አስተርጉሞ አሳትሟል፡፡

# የተባበሩት መንግሥታት የንግድ እና ሰብአዊ መብቶች መመሪያ መርሖች

## አጠቃላይ መርሖች

እነዚህ የመመሪያ መርሖች፡-

(ሀ) ሰብአዊ መብቶችን እና መሠረታዊ ነጻነቶችን የማክበር፣ የመጠበቅና የማሟላት ነባር የመንግሥት ግዴታዎችን፤

(ለ) የንግድ ድርጅቶች እንደ ልዩ የኅብረተሰብ አካል ልዩ ተግባራትን የማከናወን ሚና ሲወጡ ሁሉንም የሚመለከታቸው ሕጎችን እና ሰብአዊ መብቶችን በማክበር እንዲሆን ተጠባቂነትን፤

(ሐ) መብቶች እና ግዴታዎች በሚጣሱበት ጊዜ ተገቢና ውጤታማ ከሆኑ መፍትሔዎች ጋር እንዲጣጣሙ የማድረግ አስፈላጊነትን ዕውቅና በመስጠት የተመሠረቱ ናቸው።

እነዚህ የመመሪያ መርሖች ለሁሉም ሀገራት እና መጠናቸው፣ የተሰማሩበት ዘርፍ፣ ቦታቸው፣ ባለቤትነታቸው እና መዋቅራቸው ምንም ይሁን ምን ለሁሉም ድንበር ተሻጋሪ እና ሌሎች የንግድ ድርጅቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

እነዚህን የመመሪያ መርሖች አንድ ወጥነት ባለው መልኩ መረዳት እና በተናጠልም ሆነ በጋራ ሲነበቡ ከንግድ እና ሰብአዊ መብቶች ጋር በተያያዘ ደረጃዎችን እና አሠራሮችን በማጎልበት ለተጎዱ ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች ተጨባጭ ውጤቶችን ለማምጣት እና በዚህም ማኅበራዊ ዘላቂነት ላለው ግሎባላይዜሽን አስተዋጽዖ በሚያደርግ መልኩ መሆን አለበት።

እነዚህ የመመሪያ መርሖች አዲስ የዓለም አቀፍ ሕግ ግዴታዎችን እንደሚፈጥሩ፣ ወይም አንድ ሀገር ሰብአዊ መብቶችን በሚመለከት በዓለም አቀፍ ሕግ የገባውን ወይም የተጣለበትን ማንኛውንም ሕጋዊ ግዴታን የሚገድብ ወይም የሚያዳክም ተደርጎ መነበብ የለበትም።

እነዚህ መመሪያ መርሖች ከፍተኛ የተጋላጭነት ወይም የመገለል ሥጋት ሊደርስባቸው የሚችሉ ቡድኖች ወይም ሕዝቦች አባል የሆኑ ግለሰቦችን መብቶች እና ፍላጎቶች፣ እንዲሁም የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን የተለየ ትኩረት በሰጠ፣ እና በሴቶች እና በወንዶች ላይ ሊደርሱ ስለሚችሉ የተለያዩ አደጋዎችን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ያለአድልዎ መተግበር አለባቸው።

# I. ሰብአዊ መብቶችን የመጠበቅ የመንግሥት ግዴታ

## *ሀ. መሠረታዊ መርሖች*

1. ***መንግሥታት በግዛታቸው እና/ወይም በሥልጣናቸው ሥር የንግድ ድርጅቶችን ጨምሮ በሦስተኛ ወገን የሚደርስ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መጠበቅ አለባቸው። ይህም ውጤታማ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ሕግን፣ ደንቦችን እና የፍርድ ውሳኔን በመጠቀም የዚህ ዓይነቱን ጥሰት ለመከላከል፣ ለመመርመር፣ ለመቅጣት እና ለማስተካከል ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድን ይጠይቃል።***

***ማብራሪያ***

*ሀገራት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግ ያለባቸው ግዴታዎች በግዛታቸው እና/ወይም በሥልጣናቸው ሥር የሚገኙ ግለሰቦችን ሰብአዊ መብቶች እንዲያከብሩ፣ እንዲጠብቁ እና እንዲያሟሉ ይጠይቃሉ። ይህም የንግድ ድርጅቶችን ጨምሮ በሦስተኛ ወገን የሚደርስ የሰብአዊ መብቶች ጥሰትን የመጠበቅ ግዴታን ያጠቃልላል።*

*የመንግሥት ሰብአዊ መብቶችን የመጠበቅ ግዴታ ቋሚ ግዴታ እና የመንግሥታት የሥነ ምግባር መለኪያ ነው። በግል ተቋማት (ተሳታፊዎች) ለሚደርስ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መንግሥታት በቀጥታ ተጠያቂ አይደሉም። ሆኖም ጥሰቱ ለመንግሥታት የሚሰጥ ከሆነ፣ ወይም በግል ተቋማት (ተሳታፊዎች) የሚፈጸምን ጥሰት ለመከላከል፣ ለመመርመር፣ ለመቅጣት እና ለማስተካከል ተገቢውን እርምጃ ካልወሰዱ፣ መንግሥታት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግ ያለባቸውን ግዴታዎች ሊጥሱ ይችላሉ። በጥቅሉ ሲታይ መንግሥታት የሚወሰዱ እርምጃዎችን በመወሰን ረገድ ነጻነት ቢኖራቸውም ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችን፣ ደንቦችንና የፍርድ ውሳኔዎችን ጨምሮ የሚፈቀዱትን አጠቃላይ የመከላከያና የመፍትሔ እርምጃን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። በተጨማሪም መንግሥታት እንደ በሕግ ፊት እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመውሰድ፣ የአተገባበር ፍትሐዊነትን በማረጋገጥ፣ እና በቂ ተጠያቂነት፣ ሕጋዊ እርግጠኝነት፣ እና የአሠራርና የሕግ ግልጽነት እንዲኖር በማድረግ የሕግ የበላይነትን የመጠበቅ እና የማስፋፋት ግዴታ አለባቸው።*

ይህ ምዕራፍ ትኩረት የሚያደርገው በመከላከያ እርምጃዎች ላይ ሲሆን ምዕራፍ ሦስት ደግሞ የመፍትሔ እርምጃዎችን ይዘረዝራል።

2. **ሀገራት በግዛታቸው እና/ወይም በሥልጣናቸው ውስጥ የሚገኙ ሁሉም የንግድ ድርጅቶች በእንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ ሰብአዊ መብቶችን ማክበር እንደሚጠበቅባቸው በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል።**

**ማብራሪያ**

በአሁኑ ጊዜ በጥቅሉ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግ መሠረት ሀገራት በግዛታቸው እና/ወይም በሥልጣናቸው ውስጥ የሚገኙ የንግድ ድርጅቶችን ድንበር ዘለል እንቅስቃሴዎች እንዲቆጣጠሩ አይገደዱም። ዕውቅና ያለው የሥልጣን መሠረት ካለ ግን በአጠቃላይ ይህን እንዳያደርጉ አይከለከሉም። በእነዚህ መለኪያዎች ውስጥ፣ አንዳንድ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት ተቆጣጣሪ አካላት ሀገራት በሥልጣን ግዛታቸው ውስጥ የሚገኙ የንግድ ድርጅቶች በውጭ ሀገር የሚያደርሱትን ጥሰት ለመከላከል እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይመክራሉ።

ሀገራት በግዛታቸው የሚገኙ የንግድ ድርጅቶች ከግዛታቸው ውጪ የሰብአዊ መብቶችን እንዲያከብሩ እንደሚጠበቅ በግልጽ ለማስቀመጥ የሚያስችል ጠንካራ የፖሊሲ ምክንያቶች አሏቸው። ይህ በተለይ በእነዚህ የንግድ ድርጅቶች ውስጥ መንግሥት ራሱ በሚሳተፍበት ወይም በሚደግፍበት ጊዜ እውነት ነው። ምክንያቶቹ ወጥነት ያላቸው እና ተከታታይ የሆኑ መልዕክቶችን በማቅረብ የንግድ ድርጅቶችን ተገማችነት ማረጋገጥ፣ እና የመንግሥትን የራሱን ክብር ማስጠበቅን ያካትታሉ።

በዚህ ረገድ ሀገራት የተለያዩ መንገዶችን ይከተላሉ። አንዳንዶቹ ድንበር ዘለል አንድምታ ያላቸው የሀገር ውስጥ እርምጃዎች ናቸው። እንደ ምሳሌ እናት ኩባንያዎች ስለ አጠቃላይ የድርጅቱ ዓለም አቀፋዊ ሥራዎች ሪፖርት እንዲያደርጉ መፈለግ፤ እንደ የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት የባለ ብዙ ሀገራት ድርጅቶች መመሪያዎች ያሉ የባለብዙ ወገን አስገዳጅ ያልሆኑ ሰነዶች፤ እና የውጭ ኢንቨስትመንቶችን በሚደግፉ ተቋማት የሚፈለጉ የአፈጻጸም ደረጃዎች ይካተታሉ። ሌሎች መንገዶች ደግሞ ቀጥተኛ የድንበር ተሻጋሪ ሕግ እና አፈጻጸም ተደርገው ይወሰዳሉ። ይህም ወንጀሉ የተፈጸመው የትም ቦታ ቢሆን በወንጀለኛው ዜግነት ላይ ተመሥርቶ ክስ እንዲመሠረት

የሚፈቅዱ የወንጀል ሥርዓቶችን ያጠቃልላል። እንደ ባለብዙ ወገን ስምምነት ላይ የተመሠረቱ መሆን አለመሆናቸው ዓይነት የተለያዩ ምክንያቶች የመንግሥታት እርምጃዎችን ግምታዊ ወይም ትክክለኛ ምክንያታዊነት ላይ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ ይችላሉ።

**ለ. የአሠራር መርሖች**

**አጠቃላይ የመንግሥት የቁጥጥር እና የፖሊሲ ተግባራት**

**3. መንግሥታት የመጠበቅ ግዴታቸውን ለመወጣት፡-**

**(ሀ) የንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶችን እንዲያከብሩ የሚጠይቁትን ወይም ተጽዕኖ ያላቸውን ሕጎች ማስከበር፣ እና የእነዚህን ሕጎች በቂነት በየጊዜው በመገምገም ክፍተቶችን መሙላት፤**

**(ለ) እንደ የድርጅት ሕግ ያሉ የንግድ ድርጅቶችን አፈጣጠር እና ቀጣይነት ያለው አሠራር የሚገዙ ሌሎች ሕጎች እና ፖሊሲዎች የንግድ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን ማክበር እንዳይገድቡ ማድረግ፤**

**(ሐ) የንግድ ድርጅቶች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ሁሉ ሰብአዊ መብቶችን እንዴት ማክበር እንዳለባቸው ውጤታማ መመሪያ መስጠት፤**

**(መ) የንግድ ድርጅቶች በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ እንዴት እንደሚፈቱ እንዲያሳውቁ ማበረታታት እና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ማስገደድ፤አለባቸው።**

**ማብራሪያ**

ሀገራት የንግድ ድርጅቶች ሁልጊዜ የመንግሥት እርምጃ አለመውሰድን ይመርጣሉ ወይም ይጠቀማሉ ብለው ማሰብ የለባቸውም፤ እንዲሁም የንግድ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን ማክበርን እንዲያጎለብቱ ለማስቻል ሀገራት ብሔራዊ እና ዓለም አቀፋዊ፣ አስገዳጅ እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ የተመረጡ እርምጃዎችን ድብልቅ ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

ንግድ ሰብአዊ መብቶችን ማክበር እንዳለበት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚገዙ አሁን ያሉ ሕጎችን ተግባራዊ ማድረግ አለመቻል በመንግሥት አሠራር ውስጥ ትልቅ የሕግ ክፍተት ነው። እነዚህም አድልዎን ከሚከለክሉ

እና የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕጎች እስከ የአካባቢ፣ የንብረት፣ የግላዊነት እና ፀረ-ሙስና ሕጎችን ያካትታሉ። በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ እንዲህ ዓይነቶቹ ሕጎች ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተተገበሩ መሆን አለመሆናቸውንና፣ እየተተገበሩ ካልሆነ ደግሞ ይህ የሆነው ለምን እንደሆነ እና ሁኔታውን በምክንያታዊነት ለማስተካከል ምን እርምጃዎች ሊወሰዱ እንደሚችሉ መንግሥታት ማጤን አለባቸው።

በተመሳሳይ ሁኔታ መንግሥታት እነዚህ ሕጎች ለአዳዲስ ሁኔታዎች አስፈላጊውን ሽፋን የሚሰጡ መሆን አለመሆናቸውንና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ካላቸው ፖሊሲዎች ጋር በመሆን ንግድ ሰብአዊ መብቶችን እንዲያከብር አመቺ ሁኔታ መፍጠር አለባቸው። ለምሳሌ፣ እንደ መሬት የማግኘት መብትን በሚገዙ ሕጎች የሚካተቱ፣ ከመሬት ባለቤትነት ወይም አጠቃቀም ጋር የተያያዙ መብቶችን ጨምሮ አንዳንድ የሕግ እና የፖሊሲ መስኮች ብዙውን ጊዜ የመብቶችን ባለቤቶች እና የንግድ ድርጅቶችን ለመጠበቅ የበለጠ ግልጽ መሆን አስፈላጊ ነው።

እንደ የድርጅት እና የዋስትና ሕጎች ያሉ የንግድ ድርጅቶችን አፈጣጠር እና ቀጣይነት ያለው አሠራር የሚቆጣጠሩ ሕጎች እና ፖሊሲዎች የንግድ ባሕርይበቀጥታ ይቀርፃሉ። ሆኖም በሰብአዊ መብቶች ላይ ያላቸው አንድምታ በደንብ ግልጽ አይደለም። ለምሳሌ በድርጅት እና የዋስትና ሕግ ውስጥ የድርጅቶች እና ባለሥልጣኖቻቸው ሰብአዊ መብቶችን በሚመለከት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይቅርና የሚፈቀዱትን በተመለከተ ግልጽነት ይጎድላል። በዚህ ረገድ ያሉ ሕጎች እና ፖሊሲዎች ድርጅቶች እንደ የድርጅት ቦርድ ያሉ የአስተዳደር መዋቅሮች የሚጫወቱትን ሚና በተገቢው መንገድ በመረዳት ሰብአዊ መብቶችን እንዲያከብሩ የሚያስችል በቂ መመሪያ ሊሰጡ ይገባል።

ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር ለንግድ ድርጅቶች የሚሰጠው መመሪያ የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚጠቁም እና የተሻሉ ልምዶችን ለማጋራት የሚረዱ መሆን አለባቸው። እንዲሁም ተገቢውን የሰብአዊ መብቶች ትጋትን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ ዘዴዎችን ማሳየት፤ እና በቀደምት ሕዝቦች፣ በሴቶች፣ በኅዳጣን ብሔረሰቦች ወይም ጎሳዎች፣ በሃይማኖት እና የቋንቋ ኅዳጣኖች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ እና ስደተኛ ሠራተኞች እና ቤተሰቦቻቸው ሊገጥሟቸው የሚችሉ ፈተናዎችን በመገንዘብ፣ የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን፣ የተጋላጭነት እና/ወይም የመገለል ሁኔታን እንዴት ውጤታማ በሆነ መንገድ ማሰብ እንደሚቻል ማሳየት ይኖርባቸዋል።

የፓሪስ መርሖችን የሚያከብሩ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ሀገራት አግባብነት ያላቸው ሕጎች ከሰብአዊ መብቶች ግዴታዎቻቸው ጋር የተጣጣሙ እና በአግባቡ እየተተገበሩ መሆናቸውን ለመለየት በማገዝ፣ እና ለንግድ ድርጅቶች እና ለሌሎች መንግሥታዊ ላልሆኑ በግል ተቋማት (ተሳታፊዎች) በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ መመሪያ በመስጠት ረገድ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡

የንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎቻቸውን እንዴት እንደሚወጡ የሚገልጹበት መንገድ ከተጎዱ ባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ ያልሆነ ትስስር ከመፍጠር አንስቶ መደበኛ የሕዝብ ሪፖርት እስከማቅረብ ድረስ ሊደርስ ይችላል፡፡ መንግሥታት እንዲህ ዓይነቱን ግንኙነት መደገፋቸው ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ማስገደዳቸው በንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶች መከበር እንዲጎለብት አስፈላጊ ነው፡፡ በቂ መረጃ ለማስተላለፍ የሚደረጉ ማበረታቻዎች ውስጥ በማንኛውም የፍርድ ወይም የአስተዳደር ሂደት እንዲህ ላለው ራስን ሪፖርት ማድረግ ክብደት የሚሰጡ ድንጋጌዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡ የንግድ እንቅስቃሴዎች ዓይነት ወይም የአሠራር ሁኔታዎች በሰብአዊ መብቶች ላይ ከፍተኛ አደጋ በሚፈጥሩበት ጊዜ የማስታወቅ ግዴታ በተለይ ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ዘርፍ ያሉ ፖሊሲዎች ወይም ሕጎች የንግድ ድርጅቶች ምን እና እንዴት ማሳወቅ እንዳለባቸው በሚጠቅም መልኩ ግልጽ ሊያደርጉ የሚችሉ ሲሆን፤ ይህም የማሳወቁን ተደራሽነት እና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

በቂ ማሳወቅ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚያመላክት ማንኛውም ድንጋጌ የግለሰቦች እና መገልገያዎች ደኅንነት ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን አደጋ፤ ሕጋዊ የሆኑ የንግድ ምስጢራዊ መስፈርቶችን፤ እና በኩባንያዎች መጠን እና መዋቅሮች ላይ ያሉ ልዩነቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶች በአንዳንድ ሁኔታዎች የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች ለንግድ ድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ አፈጻጸም “መሠረታዊ” ወይም “ጉልሕ” ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ማድረግ አለባቸው፡፡

## *የመንግሥት-ንግድ ትስስር*

4. ***ሀገራት በመንግሥት ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ሥር ባሉ የንግድ ድርጅቶች፣ ወይም እንደ የወጪ ንግድ የብድር ወኪሎች እና ይፋዊ የኢንቨስትመንት መድኅን ወይም የዋስትና ተወካዮች ባሉ የመንግሥት ተወካዮች ከፍተኛ ድጋፍና አገልግሎት የሚያገኙ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶች ላይ የሚደርሰውን ጥሰት ለመከላከል ወይም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የሰብአዊ መብቶችን ተገቢ ትጋት በማሟላት ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡***

### *ማብራሪያ*

*በዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሕግ መሠረት ሀገራት በየግላቸው ተቀዳሚ ባለግዴታዎች ሲሆኑ በጋራ ደግሞ የዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሥርዓት ጠባቂዎች ናቸው፡፡ አንድ የንግድ ድርጅት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ከሆነ ወይም ተግባራቶቹ የመንግሥት እንደሆኑ በሚቆጠሩበት ጊዜ፣ በንግድ ድርጅቱ የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የመንግሥት ዓለም አቀፍ ሕግ ግዴታዎች መጣስን ሊያስከትል ይችላል፡፡ በተጨማሪም አንድ የንግድ ድርጅት ለመንግሥት ቅርብ በሆነ ቁጥር፣ አልያም በሕግ ሥልጣን ወይንም በግብር ከፋዮች ድጋፍ ላይ የበለጠ በተመሠረተ ቁጥር፣ የንግድ ድርጅቱ ሰብአዊ መብቶችን ማክበሩን ለማረጋገጥ የመንግሥት ፖሊሲ ምክንያት የበለጠ ጠንካራ እየሆነ ይሄዳል፡፡*

*መንግሥታት ባለቤት በሆኑባቸው ወይም በሚቆጣጥሯቸው የንግድ ድርጅቶች ላይ የሰብአዊ መብቶች መከበርን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ሕጎችና ደንቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያደርጉበት የተሻለ መንገድ በሥልጣናቸው ሥር አሏቸው፡፡ ከፍተኛ የአስተዳደር አካላት አብዛኛውን ጊዜ ለመንግሥት ድርጅቶች ሪፖርት የሚያደርጉ ሲሆን ከዚህ ጋር የተያያዙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውጤታማ የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት እንዲተገበር ማድረግን ጨምሮ ከፍተኛ በሆነ ጥንቃቄ የመመርመርና በበላይ የመመልከት ዐቅም አላቸው፡፡ (እነዚህ ድርጅቶች በምዕራፍ II ሥር የተገለጹት ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ድርጅታዊ ኀላፊነት አለባቸው፡፡)*

*ከመንግሥት ጋር መደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ መንገድ የሚገናኙ የተለያዩ ተወካዮች ለንግድ እንቅስቃሴዎች ድጋፍና አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡*

*ከእነዚህም መካከል የወጪ ንግድ የብድር ወኪሎች፣ ይፋዊ የኢንቨስትመንት መድኅን ወይም የዋስትና ተወካዮች፣ የልማት ድርጅቶችና የልማት ፋይናንስ ተቋማት ይገኙበታል። እነዚህ ወኪሎች በተጠቃሚ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶች ላይ በተጨባጭ የሚደርሰውንና ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት በግልጽ ካላጤኑ ራሳቸውን በመልካም ስም፣ በገንዘብ፣ በፖለቲካ እና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለአደጋ ያጋልጣሉ፤ እንዲህ ዓይነቱን ጉዳት በመደገፍ፣ እንዲሁም ተቀባዩ መንግሥት በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚገጥሙትን ተግዳሮቶች ይበልጥ ሊጨምሩ ይችላሉ።*

*እነዚህን አደጋዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ መንግሥታት በራሳቸው ድርጅቶችና ድጋፋቸውን በሚቀበሉ የንግድ ድርጅቶች ወይም ፕሮጀክቶች ተገቢውን የሰብአዊ መብቶች ትጋት ማበረታታትና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ መጠየቅ ይኖርባቸዋል። የንግድ እንቅስቃሴዎች ባሕርይ ወይም የአሠራር ይዘት ለሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ አደጋ ሲደቅን የሰብአዊ መብቶች ተገቢ የትጋት መለኪያ ነጥቦችን ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል።*

### *የሀገራትና የንግድ ቁርኝት*

**4. *ሀገራት በመንግሥት ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ሥር ያሉ ወይም ከመንግሥት እንደ የውጭ ንግድ ብድር አገልግሎት እና የመንግሥት መድኅን ወይም የዋስትና ውክልናን የመሳሰሉ ከፍተኛ ድጋፍና አገልገሎቶችን በሚቀበሉ የንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይደርሱ አስፈላጊ ሲሆን የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት መጠየቅን ጨምሮ ተጨማሪ እርምጃዎችን በመውሰድ ጥበቃ ማድረግ አለባቸው።***

### *ማብራሪያ*

*በዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሕግ መሠረት ሀገራት በየግላቸው ተቀዳሚ ባለግዴታዎች ሲሆኑ በጋራ ደግሞ የዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሥርዓት ጠባቂዎች ናቸው። አንድ የንግድ ድርጅት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ከሆነ ወይም ተግባራቶቹ የመንግሥት እንደሆኑ በሚቆጠሩበት ጊዜ፣ በንግድ ድርጅቱ የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የመንግሥት ዓለም አቀፍ ሕግ ግዴታዎች መጣስን ሊያስከትል ይችላል። በተጨማሪም አንድ የንግድ ድርጅት ለመንግሥት ቅርብ በሆነ ቁጥር፣ አልያም በሕግ ሥልጣን ወይንም በግብር ከፋዮች ድጋፍ ላይ የበለጠ በተመሠረተ ቁጥር፣ የንግድ ድርጅቱ*

ሰብአዊ መብቶችን ማክበሩን ለማረጋገጥ የመንግሥት ፖሊሲ ምክንያት የበለጠ ጠንካራ እየሆነ ይሄዳል።

መንግሥታት ባለቤት በሆኑባቸው ወይም በሚቆጣጠሯቸው የንግድ ድርጅቶች ላይ የሰብአዊ መብቶች መከበርን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ሕጎችና ደንቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያደርጉበት የተሻለ መንገድ በሥልጣናቸው ሥር አሏቸው። ከፍተኛ የአስተዳደር አካላት አብዛኛውን ጊዜ ለመንግሥት ድርጅቶች ሪፖርት የሚያደርጉ ሲሆን ከዚህ ጋር የተያያዙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውጤታማ የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት እንዲተገበር ማድረግን ጨምሮ ከፍተኛ የሆነ በጥንቃቄ የመመርመርና በበላይ የመመልከት ዐቅም አላቸው። (እነዚህ ድርጅቶች በምዕራፍ II ሥር የተገለጹት ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ድርጅታዊ ኀላፊነት አለባቸው።)

ከመንግሥት ጋር መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ የሚገናኙ የተለያዩ ተወካዮች ለንግድ እንቅስቃሴዎች ድጋፍና አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል የወጪ ንግድ የብድር ወኪሎች፣ መንግሥታዊ የኢንቨስትመንት መድኅን ወይም የዋስትና ተወካዮች፣ የልማት ድርጅቶችና የልማት ፋይናንስ ተቋማት ይገኙበታል። እነዚህ ወኪሎች በተጠቃሚ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶች ላይ በተጨባጭ የሚደርሰውንና ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት በግልጽ ካላጤኑ ራሳቸውን በመልካም ስም፣ በገንዘብ፣ በፖለቲካ እና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለአደጋ ያጋልጣሉ፤ እንዲህ ዓይነቱን ጉዳት በመደገፍ፣ እንዲሁም ተቀባዩ መንግሥት በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚገጥሙትን ተግዳሮቶች ይበልጥ ሊጨምሩ ይችላሉ።

እነዚህን አደጋዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ መንግሥታት በራሳቸው ድርጅቶችና ድጋፋቸውን በሚቀበሉ የንግድ ድርጅቶች ወይም ፕሮጀክቶች የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት ማበረታታትና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ መጠየቅ ይኖርባቸዋል። የንግድ እንቅስቃሴዎች ባሕርይ ወይም የአሠራር ይዘት ለሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ አደጋ ሲደቅን የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት መለኪያ ነጥቦችን ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል።

**5. *ሀገራት በሥራቸው በሰብአዊ መብቶች መከበር ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ የንግድ ድርጅቶች ጋር ሲዋዋሉ ወይም ሕግ ሲያወጡላቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎችን ለመወጣት በቂ ቁጥጥር ማድረግ አለባቸው።***

***ማብራሪያ***

*ሀገራት በሰብአዊ መብቶች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ አገልግሎቶችን ወደ ግል ማዘዋወራቸው በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች የተጣለባቸውን ግዴታ ቀሪ አያደርገውም። እንደዚህ ያሉ አገልግሎቶችን የሚያከናውኑ ድርጅቶች አሠራር ከሰብአዊ መብቶች ጋር የተጣጣሙ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አለመቻል በሀገራት ላይ የመልካም ሥም እና ሕጋዊ ውጤቶችን ሊያስከትል ይችላል። አግባብነት ያለው የአገልግሎት ውል ወይም አስቻይ ሕግ እንደ አስፈላጊ እርምጃ በመንግሥታት የሚጠበቁ ይህም እነዚህ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብሩ ስለመሆናቸው ግልጽ ማድረግ አለባቸው። ሀገራት በቂ ገለልተኛ የክትትል እና የተጠያቂነት ሥልቶች አቅርቦትን ጨምሮ የድርጅቶቹን እንቅስቃሴ በብቃት መቆጣጠር መቻላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።*

**6. *መንግሥታት የንግድ ልውውጦችን በሚያካሂዱባቸው የንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶችን እንዲያከብሩ ማስተዋወቅ አለባቸው።***

***ማብራሪያ***

*መንግሥታት ከንግድ ድርጀቶች ጋር ቢያንስ በግዥ ተግባራቸው የተለያዩ የንግድ ልውውጦችን ያካሂዳሉ። ይህ መንግሥታት በብሔራዊ እና በዓለም አቀፍ ሕጎች አግባብነት ያላቸውን ግዴታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የውል ድንጋጌዎችን ጨምሮ ድርጀቶቹ የሰብአዊ መብቶችን ግንዛቤ እና መከበርን ለማስተዋወቅ የተናጠልና የጋራ ልዩ ዕድሎች አላቸው።*

**የንግድ ድርጅቶች በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች ሰብአዊ መብቶችን እንዲያከብሩ መደገፍ**

**7. *ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሥጋት የሚጨምር በመሆኑ መንግሥታት በእነዚህ ዐውዶች ውስጥ የሚሠሩ የንግድ ድርጅቶች በጥቃቶች እንዳይሳተፉ ለማረጋገጥ በሚከተሉት ዘዴዎች ጭምር መርዳት አለባቸው፤***

**(ሀ) በተቻለ ፍጥነት ከንግድ ድርጅቶች ጋር በመሳተፍ ከሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ጋር የተያያዙ የእንቅስቃሴዎቻቸው እና የንግድ ግንኙነቶቻቸው አደጋዎችን እንዲለዩ፣ እንዲከላከሉ እና እንዲቀንሱ መርዳት፤**

**(ለ) የንግድ ድርጅቶች ከፍ ያሉ የጥሰት ሥጋቶች ለጾታ-ተኮር እና ወሲባዊ ጥቃት ልዩ ትኩረት በመስጠት ለመፍታት እንዲገመግሙ በቂ ድጋፍ መስጠት፤**

**(ሐ) በከባድ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ለተሳተፉ እና ሁኔታውን ለመፍታት ለመተባበር ፈቃደኛ ለማይሆኑ የንግድ ድርጅቶች የሕዝብ ድጋፍ እና አገልግሎቶችን መከልከል፤**

**(መ) ያላቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች እና የማስፈጸሚያ እርምጃዎች በከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተሳትፎ ሥጋትን ለመፍታት ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ።**

*ማብራሪያ*

*ከንግድ ጋር የተያያዙ አንዳንድ አስከፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የሰብአዊ መብቶች ሥርዓቱ በፈረሰበት ወይም በተዳከመበት ወቅት፣ ይዞታን፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ ሀብትን ወይም መንግሥት ለመቆጣጠር በሚደረጉ ግጭቶች ወቅት የሚከሰቱ ናቸው። ኃላፊነት የሚሰማቸው የንግድ ተቋማት በእነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት አስተዋጽዖ እንዳያደርጉ በየጊዜው ከመንግሥታት መመሪያ ማግኘት ይፈልጋሉ። አዲስ እና ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ሥልቶች ያስፈልጋሉ። በግጭት ጊዜ በተለየ መልኩ የሚፈጠረውን ጾታዊ እና ጾታን መሠረት የሚያደርጉ ጥቃቶችን ሥጋት በልዩ ሁኔታ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው።*

*ሁሉም መንግሥታት መሬት ላይ ያሉ ሁኔታዎች ከመባባሳቸው በፊት አስቀድመው መፍታት መቻላቸው አስፈላጊ ነው። ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች "ተቀባዩ" ሀገር ውጤታማ ቁጥጥር ባላማድረጋቸው ሰብአዊ መብቶችን በበቂ ሁኔታ ማስጠበቅ አይችሉ ይሆናል። ድንበር ተሻጋሪ ድርጅቶች በሚሳተፉበት ቦታ የንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ውስጥ እንደማይሳተፉ ለማረጋገጥ "ላኪ" ሀገራት ሁለቱንም ማለትም ድርጅቶችን እና ተቀባይ ሀገርን ለመርዳት ሚናዎች አሏቸው፤ አጎራባች ሀገራት ደግሞ ጠቃሚ ተጨማሪ ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ።*

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ የበለጠ የፖሊሲ ወጥነት ለማምጣት እና የንግድ ድርጅቶችን በበቂ ሁኔታ ለመርዳት ተቀባይ መንግሥታት ከልማት እርዳታ ድርጅቶች ከውጭ ጉዳይ እና ንግድ ሚኒስቴር፣ በዋና ከተማዎቻቸው እና በኤምባሲዎቻቸው ውስጥ የሚገኙ የውጭ ንግድ የፋይናንስ ተቋማትን እንዲሁም በእነዚህ ተቋማት እና የተቀባይ መንግሥት በግል ተቋማት (ተሳታፊዎች) የበለጠ መቀራረብ አለባቸው፤ የመንግሥት ተቋማት እና የንግድ ድርጅቶችን የችግሮች ቅድመ ማስጠንቀቂያ አመልካቾች ማዳበር፤ እና በዚህ ዐውድ ላለው ለማንኛውም የድርጅቶች መተባበር አለመቻል ያለውን የሕዝብ ድጋፍ ወይም አገልግሎቶችን መከልከል ወይም ማውጣት ወይም ይህ የሚቻል ካልሆነ የወደፊት አቅርቦታቸውን መከልከልን ጨምረው ተገቢውን ውጤት መስጠት መቻል አለባቸው፡፡

መንግሥታት ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ጋር የተያያዘ የንግድ ድርጅቶችን ተሳትፎ ሥጋትን ከፍ አድርገው ማስጠንቀቅ አለባቸው፡፡ ፖሊሲዎቻቸውን፣ ሕጋቸውን፣ ደንቦቻቸውን እና የማስፈጸሚያ እርምጃዎች ይህን ከፍተኛ ሥጋትን በብቃት መቅረፍ መቻላቸውን በንግድ ሥራ የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት አቅርቦትን ጨምሮ መገምገም አለባቸው፡፡ መንግሥታት ክፍተቶችን ሲለዩ እነዚህን ለመፍታት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡

ይህ በግዛታቸው እና/ወይም በኃላፊነታቸው ውስጥ የሚኖሩ ወይም የሚሠሩ ከባድ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በሚፈጽሙ ወይም አስተዋጽዖ በሚያደርጉ ድርጀቶች ላይ የፍትሐብሔር፣ የአስተዳደር ወይም የወንጀል ተጠያቂነትን ማሰስን ሊያካትት ይችላል፡፡ ከዚህም በላይ መንግሥታት መሰል ድርጊቶችን ለመከላከል እና ለመፍታት የብዝኃ ወገን አቀራረቦችን ያቀፉ ውጤታማ የጋራ ተነሳሽነት ድጋፍን ማሰብ አለባቸው፡፡

እነዚህ ሁሉ እርምጃዎች በትጥቅ ግጭት ሁኔታዎች በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ እና የወንጀል ሕግ ከመንግሥታት ግዴታዎች በተጨማሪ ናቸው፡፡

### የፖሊሲ ወጥነትን ማረጋገጥ

**8. ሀገራት የመንግሥት የሥራ ክፍሎች፣ ኤጀንሲዎች እና ሌሎች በመንግሥት ላይ የተመሠረቱ የንግድ አሠራሮችን የሚቀርጹ ተቋማት የየራሳቸውን ኀላፊነቶች ሲፈጽሙ የመንግሥትን የሰብአዊ መብቶች**

**ግዴታዎችን በማወቅ መረጃ፣ ስልጠና እና ድጋፍ ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን ነገሮች ማቅረባቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡**

*ማብራሪያ*

በሀገራት የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች እና የንግድ አሠራርን በሚቀርጹ ሕጎች እና ፖሊሲዎች መካከል ሊታረቅ የማይችል አለመጣጣም ሊክሰት አይችልም፡፡ ሆኖም ግን ሀገራት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ፍላጎቶችን ለማስታረቅ ሚዛናዊ ውሳኔዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡ ትክክለኛውን ሚዛን ለማግኘት ንግዱን እና የሰብአዊ መብቶችን አጀንዳ ለማስተዳደር ሀገራት ሰፊ አቀራረብ በመውሰድ ሁለቱንም አቀባዊ እና የጎንዮሽ የሀገር ውስጥ የፖሊሲ ወጥነትን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

አቀባዊ የፖሊሲ ወጥነት አስፈላጊ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች እና ሂደቶች የመንግሥታትን የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ የጎንዮሽ የፖሊሲ ወጥነት ማለት በሀገር እና በንዑስ ብሔራዊ ደረጃዎች፣ የንግድ ልምዶችን የሚቀርጹ ለድርጅት የሕግ ተጠያቂ የሆኑትን እና የዋስትና ደንቦች፣ ኢንቨስትመንት፣ የውጭ ንግድ ብድር እና ዋስትና፣ ንግድ እና የጉልበት ሥራን ጨምሮ፣ የሚገኙትን የሥራ ክፍሎችን እና ተቋማት የመንግሥት የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎችን ማሳወቅ እና በሚስማማ መንገድ መሥራት ላይ መደገፍ እና ማስቻል ማለት ነው፡፡

**9. ሀገራት የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎቻቸውን ለማሟላት ከሌሎች ሀገራት ጋር ወይም የንግድ ድርጅቶች ጋር ከንግድ ጋር የተያያዘ የፖሊሲ አላማዎችን በሚከተሉበት ጊዜ ለምሳሌ በኢንቨስትመንት ስምምነቶች ወይም ውሎች በቂ የሆነ ቦታ ሀገር ውስጥ ፖሊሲ መስጠት አለባቸው፡፡**

*ማብራሪያ*

በሀገራት መካከል ወይም ሀገራት ከንግድ ድርጅቶች ጋር የሚደረጉ እንደ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች፣ የነጻ ንግድ ስምምነቶች ወይም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ውል ለሀገራት ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን ይፈጥራሉ፡፡ ነገር ግን የሀገር ውስጥ የመንግሥታት የፖሊሲ ቦታ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንት ስምምነቶች ሀገራት አዳዲስ ሰብአዊ መብቶችን ሙሉ በሙሉ እንዳይተገብሩ ሊገድቧቸው ይችላሉ ወይም የዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት አስገዳጅነት ሥጋት ላይ ይጥላቸዋል፡፡ ስለዚህ መንግሥታት በቂ ፖሊሲ መያዛቸውን በማረጋገጥ

በነዚህ ስምምነቶች መሠረት ሰብአዊ መብቶችን የመጠበቅ ቁጥጥር ችሎታ ኖሮአቸው አስፈላጊውን የባለሀብቶች ጥበቃ ማድረግ አለባቸው።

**10. *ሀገራት ከንግድ ሥራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የብዙኃን ተቋማት አባላት ሆነው ሲሠሩ ፡-***

***(ሀ) ተቋማቱ የአባል ሀገራትን የመጠበቅ ግዴታቸውን የመወጣት ችሎታ እንደማይገድቡ እንዲሁም የንግድ ድርጅቶችን ሰብአዊ መብቶችን ከማክበር እንደማያደናቅፉ ማረጋገጥ፤***

***(ለ) እነዚያን ተቋማት እንደየሥልጣናቸው እና ዐቅማቸው በንግድ ሥራ ሰብአዊ መብቶችን መከበርን እንዲያስተዋውቁ ማበረታታት፣ በተጠየቁ ጊዜ ደግሞ የቴክኒክ ድጋፍ፣ የዐቅም ግንባታ እና የግንዛቤ ማስጨበጫን ጨምሮ ሀገራት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በንግድ ድርጅቶች እንዳይፈጸሙ የመጠበቅ ግዴታቸውን እንዲወጡ መርዳት፤***

***(ሐ) በእነዚህ የመመሪያ መርሖዎች ላይ የጋራ ግንዛቤን ለማስፋፋት እና በዓለም አቀፍ ትብብር የንግድ እና የሰብአዊ መብቶች ተግዳሮቶች አስተዳደር ውስጥ ማሳደግ አለባቸው።***

***ማብራሪያ***

*መንግሥታት ከንግድ ነክ ጉዳዮች ጋር በሚገናኙ እንደ ዓለም አቀፍ ንግድ እና የፋይናንስ ተቋማት ባሉ የብዝሃን ተቋማት ውስጥ የሚሳተፉበትን ጨምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ የላቀ የፖሊሲ ወጥነት ያስፈልጋል። ሀገራት በእንደዚህ ዓይነት ተቋማት ውስጥ በሚሳተፉበት ጊዜ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግ ግዴታቸውን ይይዛሉ።*

*በመሰል ተቋማት በኩል ዐቅምን ማጎልበት እና ግንዛቤን ማሳደግ የሀገራትን የመጠበቅ ግዴታቸውን እንዲወጡ ለመርዳት ስለተግዳሮቶች እና ምርጥ ተሞክሮዎች መረጃ መጋራትን ማስቻል ለሁሉም ሀገራት የበለጠ ተከታታይ አቀራረቦችን የማስተዋወቅ ወሳኝ ሚና መጫወት ይችላል።*

*በብዝሃን ወገን ተቋማት በኩል የሚደረግ የጋራ እርምጃ ሀገራት ሰብአዊ መብቶች መከበር ጋር በተያያዘ የኀላፊነት ሥፍራ ደረጃ ለመስጠት ይረዳል፤ ነገር ግን የዘገዩትን አፈጻጸም በማሳደግ የሚደረግ መሆን አለበት።*

በሀገራት መካከል ያለው ትብብር፣ የብዝሃ ወገን ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ጠቃሚ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።

እነዚህ የመመሪያ መርሖች በዚህ ረገድ የጋራ ማጣቀሻ ነጥብ እና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ሁሉ ሚናዎች እና ኀላፊነቶች ግምት ውስጥ ያስገባ ድምር አዎንታዊ ተጽዕኖን ለመገንባት እንደ ጠቃሚ መሠረት ሆነው ያገለግላሉ።

## II. የንግድ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነት

### *ሀ. መሠረታዊ መርሖች*

**11. የንግድ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን ማክበር አለባቸው። ይህም ማለት የሌሎችን ሰብአዊ መብቶች ከመጣስ መቆጠብ እና በእነሱ ተሳትፎ ምክኒያት ለሚደርሱ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል።**

*ማብራሪያ*

ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነት የትም ቦታ ይሥሩ ከሁሉም የንግድ ድርጅቶች የሚጠበቅ ዓለም አቀፍ የአሠራር መስፈርት ነው። ይህ የአሠራር መስፈርት ከሀገራት ሰብአዊ መብቶችን የማሟላት ግዴታቸውን የመወጣት ዐቅም እና ፍላጎት ጋር ሳይገናኝ እራሱን ችሎ የሚኖር ሲሆን የሀገራትን ሰብአዊ መብቶችን የማሟላት ግዴታዎች የሚያሳንስ ወይም የሚቀንስ አይደለም። ከዚህም በላይ ለሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ለሚያደርጉ ብሔራዊ ሕጎች እና መመሪያዎች ከመገዛትም በላይ የሚኖር ነው።

ለአሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች ምላሽ መስጠት አሉታዊ ተጽዕኖዎቹን ለመከላከል፣ ለመቀነስ እና እንደአግባብነቱ መፍትሔ ለማበጀት በቂ እርምጃዎችን መውሰድ ይፈልጋል።

የንግድ ድርጅቶች መብቶችን ለመጠቀም አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ የሚችሉ የሰብአዊ መብቶችን የመደገፍ እና የማስፋፋት ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችላሉ። ይህ ማለት ግን ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ሂደት ሰብአዊ መብቶችን ሳያከብሩ ቢቀሩ እንደማካካሻ ሊያገለግላቸው ይችላል ማለት አይደለም።

የንግድ ድርጅቶች የሀገራትን የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች የመወጣት አቅም ሊሸረሽሩ አይገባም፡፡ ይህም የፍርድ ቤቶች ዳኝነት ሂደቶችን ተአማኒነት ሊያዳክሙ ከሚችሉ ድርጊቶች መቆጠብን ይጨምራል፡፡

**12. የንግድ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነት ሲባል ቢያንስ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙትን የሰብአዊ መብቶችን ማለትም በሁሉን አቀፉ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ፣ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን እና የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን እና በዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት የሥራ ላይ መሠረታዊ መርሖች እና መብቶች መግለጫ ላይ የተዘረዘሩ መብቶችን ያመለክታል፡፡**

***ማብራሪያ***

የንግድ ድርጅቶች በጠቅላላው በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ባገኙት ሁሉም የሰብአዊ መብቶች ላይ ተጽዕኖ ሊኖራቸው ስለሚችል፣ ሰብአዊ መብቶችን የማክብር ኀላፊነታቸው ሁሉንም የሰብአዊ መብቶች ይመለከታል፡፡ በተግባር፣ በተወሰኑ ኢንዱስትሪዎች እና ሁኔታዎች የተወሰኑ የሰብአዊ መብቶች ከሌሎች አንጻር ከፍተኛ አደጋ ሊኖርባቸው ስለሚችል ከፍ ያለ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ ሆኖም ግን፣ ሁኔታዎች ሊለወጡ ስለሚችሉ ሁሉም የሰብአዊ መብቶች በየጊዜው ሊገመገሙ ይገባል፡፡

አስገዳጅነት ያላቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙት አንኳር የሰብአዊ መብቶች ዝርዝር የሚገው በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነድ (ማለትም በሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ፣ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን እና የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን) እና በዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት የሥራ ላይ መሠረታዊ መብቶች እና መርሖች መግለጫ ያካተታቸው የስምንቱ ዋና ስምምነቶቹ መሠረታዊ መብቶችን የተመለከቱ መርሖች ላይ ነው፡፡ በነዚህ መስፈርቶች ነው ሌሎች ማኅበራዊ ተዋኒያን የንግድ ድርጅቶችን የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን የሚገመግሙት፡፡ የንግድ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነት በአብዛኛው እንደየአግባቡ በብሔራዊ ሕግ ድንጋጌዎች የሚወሰን ከሆነው ከሕግ ኀላፊነት እና ተፈጻሚነት የተለየ ጉዳይ ነው፡፡

የንግድ ድርጅቶች እንደየሁኔታው ተጨማሪ መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ድርጅቶቹ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን በተለዩ ቡድኖች ወይም ሕዝቦች ላይ የሚያደርሱ ከሆነ ልዩ ትኩረት በመስጠት የነዚህን ግለሰቦች መብቶች ማክበር አለባቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ የተባበሩት መንግሥታት የተለያዩ ሰነዶች የቀደምት

ነዋሪዎችን፡ የሴቶችን፤ የብሔሮችን ወይም ብሔረሰቦችን፤ የሃይማኖት እና ቋንቋ ኅዳጣንን፤ የሕፃናትን፤ የአካል ጉዳተኞችን እና የፍልሰተኛ ሠራተኞችን እና ቤተሰቦቻቸውን መብቶች በተመለከተ ተጨማሪ ማብራሪያ ይሰጣሉ። ከዚህም በላይ፣ የንግድ ድርጅቶች በትጥቅ ግጭት ወቅቶች ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕጎችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

**13. ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነት የንግድ ድርጅቶችን የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ያስገድዳል፡-**

**(ሀ) በተግባራቸው አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን ከማስከተል ወይም አስተዋጽዖ ከማድረግ መቆጠብ፣ እና ተጽዕኖዎቹ ሲከሰቱ ምላሽ እንዲሰጡ፤**

**(ለ) ምንም እንኳ ለተጽዕኖው አስተጽዖባያደርጉም ባላቸው የንግድ ግንኙነቶች ከአሠራራቸው፣ ከምርቶቻቸው ወይም ከአገልግሎታቸው ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ሁኔታ ለሚከሰቱ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ መትጋት ይጠበቅባቸዋል።**

***ማብራሪያ***

የንግድ ድርጅቶች በተግባራቸው ወይም ከሌሎች አካላት ጋር በሚያደርጉት የንግድ ግንኙነቶች አማካኝነት አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን በማድረስ ሊሳተፉ ይችላሉ። የእነዚህ ሁኔታዎች አንድምታን እና የንግድ ድርጅቶች እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው የመመሪያ መርሕ 19 ተጨማሪ ማብራሪያ ይሰጣል። ለዚህ መመሪያ መርሖች ዓላማ የንግድ ድርጅት "ተግባራት" ማድረግን እና አለማድረግን የሚያካትት፤ እና "የንግድ ግንኙነቶቹ" ደግሞ ከንግድ አጋሮች፣ በግብይት ሰንሰለቱ ውስጥ ካሉ አካላት፣ እና ከንግድ አሠራሮቹ፣ ምርቶቹ እና አገልግሎቶቹ ጋር በቀጥታ የተገናኘ ሌላ ማንኛውንም መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆነ አካል ጋር ያለ ግንኙነትን እንደሚያጠቃልል መረዳት ይገባል።

**14. ሁሉም የንግድ ድርጅቶች መጠናቸው፣ ዘርፋቸው፣ የሚሠሩበት ዐውድ፣ ባለቤትነት እና መዋቅራቸው ምንም ይሁን ምን ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነት በሁሉም ላይ ተፈጻሚ ነው። ሆኖም ግን፣ ድርጅቶቹ ይህንን ኀላፊነት የሚወጡበት መንገድ መጠን እና ውስብስብነት በነዚህ ምክንያቶች እና የንግድ ድርጅቱ እንዳስከተለው አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖ ክብደት ሊለያይ ይችላል።**

***ማብራሪያ***

የንግድ ድርጅቱ ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነቱን የሚወጣበት መንገድ በተለየ ከድርጅቱ መጠን ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይኖርበታል። አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች በዐቅም ያነሱ እና ሂደቶቻቸው እና የአስተዳደር መዋቅራቸው ከትልልቅ ኩባንያዎች ጋር ሲነጻጸር ይበልጥ ኢ-መደበኛ በመሆኑ ፖሊሲዎቻቸው እና ሂደቶቻቸው የተለያዩ ቅርጾችን ሊይዙ ይችላሉ። ነገር ግን፣ የተወሰኑ አንስተኛ እና መካከለኛ መጠን ያላቸው የንግድ ድርጅቶች ከባድ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች ሊኖራቸው ስለሚችል፣ መጠናቸው ምንም ይሁን ምን ተነጻጻሪ እርምጃዎችን መውሰድ ሊኖርባቸው ይችላል። የተጽዕኖዎቹ ክብደት የሚወሰነው በተጽዕኖው መጠን፣ ወሰን እና በማይታረም ባሕሪው ነው። በተጨማሪም የንግድ ድርጅቱ ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነቱን የሚወጣበት መንገድ የንግድ ሥራው በቡድን ወይም በግለሰብ ድርጅት መከናወኑ ላይም መሠረት በማድረግ ሊለያይ ይችላል። ነገር ግን፣ ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነት ሙሉ በሙሉ እና በእኩልነት በሁሉም የንግድ ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**15. ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነታቸውን ለመወጣት የንግድ ድርጅቶች የሚከተሉትን ጨምሮ ለመጠናቸው እና ላሉበት ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል።**

***ሀ. ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነታቸውን ለመወጣት የፖሊሲ ቁርጠኝነትን ማሳየት፤***

***ለ. የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኗቸውን መፍታት ይቻል ዘንድ ተጽዕኖዎችን ለመለየት፣ ለመከላከል፣ ለመቀነስ እና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሰብአዊ መብቶች ተገቢው ትጋት ሂደትን ማከናወን፤***

***ሐ. ያስከተሉትን ወይም አስተዋጽዖ ያደረጉበትን የትኛውንም የሰብአዊ መብቶች አሉታዊ ተጽዕኖን ለማረም የሚያስችሉ ሂደቶችን መዘርጋትን ይጨምራል።***

*ማብራሪያ*

የንግድ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን ማክበር እንዳለባቸው ማወቅ እና እንደሚያከብሩ ማሳየት አለባቸው። ይህን ማድረግ የሚችሉት የተለዩ ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን ሲዘረጉ ብቻ ነው። ከመርሕ 16 እስከ መርሕ 24 ይህን ጉዳይ የበለጠ ያብራራሉ።

**ለ. የአሠራር መርሖች**

**የፖሊሲ ቁርጠኝነት**

**16. የንግድ ደርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነታቸውን ለማካተት መነሻ የሚሆን፣ ኀላፊነታቸውን ለመወጣት ቁርጠኝነታቸውን ለመግለጽ የፖሊሲ መግለጫቸው፡**

**ሀ. በንግድ ድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ደረጃ መጽደቅ፤**

**ለ. አግባብነት ባለው በውስጥ እና በውጪ እውቀት የተመራ፤**

**ሐ. የድርጅቱ ሠራተኞችን፣ የንግድ አጋሮችን እና ሌሎች ከሥራው፣ ከምርቶቹ እና ከአገልግሎቶቹ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው አካላትን የሚመለከቱ ከደርጅቱ የሚጠበቁ ሰብአዊ መብቶችን የሚደነግግ፤**

**መ. በይፋ የሚገኝ እና በውስጥም በውጪም ላሉ ለሁሉም ሠራተኞች፣ ለንግድ አጋሮች እና ለሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት የተዋወቀ፤**

**ሰ. በመላው የንግድ ድርጅቱ የአሠራር ፖሊሲዎች እና ሂደቶች ወስጥ መካተቱን የሚያጸባርቅ መሆን አለበት።**

**ማብራሪያ**

“መግለጫ” የሚለው ቃል በጥቅል ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የንግድ ድርጅቱ ኀላፊነቶቹን፣ ቁርጠኝነቱን እና የሚጠበቁበትን ጉዳዮችን በይፋ ለማሳወቅ የሚጠቀምበትን ማንኛውንም ነገር የሚገልጽ ነው።

የፖሊሲ መግለጫው በቂነትን ለመወሰን የሚፈለገው የእውቀት ደረጃ በንግድ ድርጅቱ የአሠራር ውስብስብነት ደረጃ ሊለያይ ይችላል። እውቀቱ ተአማኒ ከሆኑ የበየነመረብ ወይም የተጻፉ ምንጮች እንዲሁም እውቅና ያለውን ባለሙያ በማማከር ሊገኝ የሚችል ነው።

የቁርጠኝነት መግለጫው በይፋ የሚገኝ መሆን አለበት። ከድረጅቱ ጋር የውል ግንኙነት ላላቸው፣ የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎችን፣ ኢንቬስተሮችን ጨምሮ ሌሎች ከድርጀቱ የሥራ ክንውን ጋር በቀጥታ ግንኙነት ላላቸው አካላት እና ጉልህ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ሥጋቶችን የሚፈጥሩ የድርጅቱ ክንውኖች ባሉበት ወቅት ተጎጂ ለሆኑ ባለድርሻ አካላት መግለጫውን በንቃት ማሳወቅ አለበት።

*መግለጫውን፣ ተዛማጅ ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን ውስጣዊ የማስተዋወቅ መንገድ የተጠያቂነት መስመሮች እና ሥርዓቶች ምን እንደሆኑ ግልጽ ማድረግ ይኖርበታል። የሚመለከታቸው የንግድ ተግባራት ሠራተኞችም በተገቢው ስልጠና ሊታገዙ ይገባል።*

*መንግሥታት ለፖሊሲ ቅንጅት እና ወጥነት እንደሚሠሩ ሁሉ፣ የንግድ ድርጅቶችም እንዲሁ ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነታቸውን እና ሰፊውን የንግድ ተግባራቸውን እና ግንኙነታቸውን የሚገዙ ፖሊሲዎች እና ሂደቶች መካከል ወጥነት እንዲኖር መጣር አለባቸው። ይህም ለምሳሌ የገንዘብ እና ሌሎች የሥራ አፈጻጸም ማበረታቻዎችን የሚወስኑ ፖሊሲዎች እና ሥርዓቶች፣ የግዢ ልምዶች እና ሰብአዊ መብቶችን አደጋ ላይ የሚጥሉ የጉትጎታ ተግባራቸውን ሊፈትሹ ይገባል።*

*በነዚህ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው መንገዶች፣ የፖሊሲ መግለጫው ከንግድ ድርጅቱ ከፍተኛ እርከን አንስቶ በሁሉም ተግባራቱ ውስጥ ሊካተት ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን ተግባራቸውን ያለ ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ ወይም ሰብአዊ መብቶችን ባላገናዘበ መልኩ ይፈጽማሉ።*

**የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት**

**17. አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖቻቸውን ለመለየት፣ ለመከላከል፣ ለመቀነስ እና ተጠያቂነትን አስፍኖ መፍትሔ ለመስጠት የንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት ሊያከናውኑ ይገባል። ይህ ሂደት ተጨባጭ እና ሊደርሱ የሚችሉ ሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን መገምገም፣ ግኝቶችን ማቀናጀት እና በግኝቶቹ መሠረት እርምጃ መውሰድ፣ ምላሾችን መከታተል እና ተጽዕኖቹ እንዴት እንደተፈቱ ማሳወቅን ሊያካትት ይገባል። የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት፡**

**ሀ. የንግድ ድርጅቱ ተግባራት ያስከተሉት ወይም አስተዋፆ ያደረጉት ወይም ከሥራዎቹ፣ ምርቶቹ ወይም አገልግሎቶቹ እና ከንግድ ግንኙነቶቹ ጋር በቀጥታ የተገናኙ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን ሊሸፈን ይገባል፤**

**ለ. ከንግድ ድርጅቱ መጠን እና ውስብስብነት፣ ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖ፣ ከሥራው ባሕርይ እና ዐውድ የተነሳ ሊለያይ ይችላል።**

**ሐ. ቀጣይነት ያለው መሆኑን፣ በጊዜ ሂደት የንግድ ድርጅቱ ሥራዎች እና የሚሠራበት ዐውድ ጋር የሰብአዊ መብቶች ሥጋቶችም እንደሚለወጥ መገንዘብ ያስፈልጋል።**

*ማብራሪያ*

ይህ መርሕ የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት መለኪያዎችን የሚገልጽ ሲሆን ከመርሕ 18 ጀምሮ እስከ መርሕ 21 ያሉት ድግሞ መሠረታዊ ይዘቶቹን ያብራራሉ።

የሰብአዊ መብቶች ሥጋቶች የንግድ ድርጅቱ ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች ሆነው ይታመናሉ። ሊከሰቱ የሚችሉ ተጽዕኖዎች በመከላከል ወይም በመቀነስ መታረም ያለባቸው ሲሆን ተጨባጭ ተጽዕኖዎች ቀድሞ በርግጥም የተከሰቱ በመሆናቸው በመፍትሔ የሚፈቱ ይሆናሉ። (መርህ 22)

የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት በንግድ ድርጅቱ የሥጋት አስተዳደር ሥርዓቶች ውስጥ መካተት የሚችል ሲሆን የኩባንያውን ቁሳዊ ሥጋቶች ከመለየት እና ከመፍታት ባሻገር የባለመብቶችን ሥጋቶችንም ሊያካትት ይገባል።

አዲስ ተግባር በሚጀመርበት ወይም አዲስ ግንኙነት በሚመሠረትበት ወቅት በተቻለ ዐቅም ከመተግበሩ በፊት የሰበአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት ሊተገበር ይገባል። ይህም የሆነበት ምክንያት የሰብአዊ መብቶች ሥጋቶች ውሎች ወይም ሌላ ስምምነቶች በሚዋቀሩበት ወቅት ሊጨምሩ ወይም ሊቀንሱ ስለሚችሉ እና የንግድ ድርጅቶች በሚዋሃዱበት ወይም በግዢ ሲተላለፉ ሥጋቶቹ አብረው ሊወረሱ ስለሚችሉ ነው።

የንግድ ድርጅቶች በእሴት/በግብይት ሰንሰለታቸው በርካታ አካላት ያሉ ሲሆን አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን ለመለየት በሁሉም ደረጃ ተገቢ ትጋት ማድረግ አስቸጋሪ ይሆናል። እንደዛ ሲሆን አቅራቢዎች ወይም ደምበኞች የሚሠሩበትን ዐውድ በተለይም የተካተቱትን አሠራሮች፣ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች በማየት በጣም ከፍተኛ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖ ሥጋት ያለባቸውን ጠቅላላ አካባቢዎች መለየት እና ለነዚህ ቅድሚያ በመስጠት የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት ማከናወን ይገባል።

የአባሪነት ጥያቄዎች የሚነሱት አንድ የንግድ ድርጅት ሌላ የንግድ ድርጅት ላስከተለው አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖ አስተዋጽ*ዖ* ያደረገ ወይም ሲያድርግ የተገኘ ሲሆን ነው። አባሪነት የሕግ እና የሕግ ያልሆነ ሁለት ትርጉሞች አሉት። እንደ የሕግ ያልሆነ ጉዳይ የንግድ ድርጅቶች እንደ 'አባሪ' የሚቆጠሩት ለምሳሌ በሌላ አካል በሚፈጸም በደል ሲጠቀሙ ሲታዩ ነው።

እንደ የሕግ ጉዳይ አብዛኞቹ ሀገራት ወንጀል በመፈጸም ረገድ አባሪነትን የሚከለክሉ ሲሆን፣ በርካቶች ደግሞ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች የንግድ

ድርጅቶችን የወንጀል ተጠያቂነትን ይፈቅዳሉ። ምንም እንኳ በሰብአዊ መብቶች ቃላት የተቀረጹ ባይሆኑም በተለምዶ የፍትሐብሔር ክሶችም የሚመሠረቱት ድርጅቱ ለጉዳቱ አስተዋጽዖ አድርጓል በሚል መነሻ ነው። የዓለም አቀፍ የወንጀል ሕግ ሚዛን ጽንሰ ሐሳብ እንደሚያመላክተው ወንጀል እንዲፈጸም መርዳት እና ማበረታታት መኖሩን ለመወሰን የምንጠቀመው አግባብነት ያለው መስፈርት በወንጀል አፈጻጸሙ ተጨባጭ ውጤት ያላውን ተግባራዊ እርዳታ እና ማበረታቻ እያወቁ ማድረግ ነው።

ተገቢውን የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት ማከናወን የንግድ ድርጅቶች በሰብአዊ መብቶች ጥሰት ላይ ላለመሳተፍ ምክንያታዊ የሆኑ እያንዳንዱን እርምጃ መውሰዳቸውን በማሳየት ሊፈጠር የሚችለውን በሕግ የመከሰስ ሥጋትን ለማስቀረት ያግዛቸዋል። ይሁን እንጂ ይህን ማድረጋቸው በራሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በማድረስ ወይም ለጥሰቶቹ አስተዋጽዖ በማድረግ የሚመጣባቸውን ተጠያቂነት በራሱ እና ሙሉ በሙሉ የሚያስቀር ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

**18. የንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶች ሥጋቶችን ለመለካት፣ በተግባራቸው ወይም በንግድ ግንኙነታቸው የተፈጠሩ እና ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን መለየት እና መገምገም አለባቸው። ይህ ሂደት፡**

***ሀ. በውስጥ እና/ወይም በገለልተኛ ውጫዊ የሰብአዊ መብቶች ዕውቀት ላይ የተመሠረተ፣***

***ለ. ለንግድ ድርጅቱ መጠንና ባሕርይ እና ለሚሠራበት ዐውድ ተገቢ የሆነ ሊጎዱ ከሚችሉ ቡድኖች እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ትርጉም ያለው ምክክር ማድረግን ያካተተ መሆን አለበት።***

***ማብራሪያ***

የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት በማድረግ ውስጥ ቀዳሚው እርምጃ የንግድ ድርጅቱ ሊሳተፍ የሚችልባቸውን የተፈጠሩ እና ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን መለየት እና መገምገም ነው። ዓላማው በአንድ በተለየ የአሠራር ዐውድ በተለዩ ሰዎች ላይ የሚኖረውን የተለዩ ተጽዕኖዎች ለመረዳት ነው። አብዛኛውን ጊዜ ይህ ከአንድ ከታቀደ የንግድ ተግባር በፊት የሰብአዊ መብቶች ዐውድን መገምገም፣ ሲቻል ተጎጂውን መለየት፣ አግባብነት ያላቸውን የሰብአዊ መብቶች መስፈርቶችን እና ጭብጦችን ስልታዊ መንገድ ማስቀመጥ እና የታቀደው የንግድ ተግባር እና

ተዛማጅ የንግድ ግንኙነቶች በተለዩት ላይ የሚኖራቸውን አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን መተንበይን ያጠቃልላል፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ የንግድ ድርጅቶች በተለይም ከቡድኑ ወይም ሕዝቡ መካከል ለሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች ከፍ ያለ ተጋላጭነት እና የመገለል ሥጋት ላለባቸው ሰዎች ልዩ ትኩረት ማድረግ የሚገባቸው ሲሆን በሴቶች እና በወንዶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የአደጋዎች ልዩነትን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

የሰብአዊ መብቶችን ተጽዕኖ የሚገመግሙ ሂደቶች እንደ ሥጋት ግምገማዎች ወይም የአካባቢ እና የማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማዎች ባሉ ሌሎች ሂደቶች ውስጥ የተካተቱ ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን ሁሉንም መብቶች እንደመመሪያ ነጥብ ሊያካትቷቸው ይገባል፡፡ ይህም የሆነበት የንግድ ድርጅቶች ከነዚህ መብቶች ውስጥ በየትኛውም መብት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ስለሚችሉ ነው፡፡

የሰብአዊ መብቶች ሁኔታዎች ተለዋዋጭ ስለሆኑ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖ ግምገማዎች በየጊዜው መከናወን አለባቸው፡፡ ከአዲስ ተግባር ወይም ግንኙነት በፊት፣ አሠራሩ ላይ መሠረታዊ ውሳኔዎች ወይም ለውጦች ከመደረጋቸው ቀድሞ (ለምሳሌ ወደ ገበያ መግባትን፣ ምርት ማሳወቅን፣ የፖሊሲ ለውጥን ወይም የንግድ ሥራው ላይ ሰፊ ለውጦችን)፣ የአሠራር አካባቢ ለውጦች ወይም ለሚጠበቁ ለውጦች ምላሽ በሚሆን መልኩ (ለምሳሌ ማኅበራዊ ውጥረቶች መነሳት) እና በየጊዜው በተግባሩ እና በግንኙነቱ ዘመን ሁሉ ሊደረግ ይገባል፡፡

የንግድ ድርጅቶቹ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኗቸውን በትክክል እንዲገመግሙ ለማስቻል ሊጎዱ የሚችሉ ባለድርሻ አካላት ሥጋቶችን ሊረዱ ይገባል፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው የቋንቋ እና ሌሎች ለውጤታማ ተሳትፎ እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ባገናዘበ መልኩ ሊጎዱ ከሚችሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቀጥታ ምክክር በማድረግ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ምክክር በማይቻልበት ሁኔታዎች የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾችን እና ሌሎች የሲቪክ ማኅበራትን ጨምሮ ተአማኒ እና ገለልተኛ የሆኑ የባለሙያ ምንጮችን እንደምክንያታዊ አማራጮች ሊጠቀሟቸው ይገባል፡፡

የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖ ግምገማው የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት ሂደት የሚቀጥለው እርምጃ ምን መሆን እንዳለበት ይጠቁማል፡፡

**19. አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን ለመከላከል እና ለማቃለል የንግድ ድርጀቶች ከተጽዕኖ ግምገማቸው የተገኙ ግኝቶችን በሚመለከታቸው**

**በውስጥ ተግባራት እና ሂደቶች በማዋሃድ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡**

**(ሀ) ውጤታማ ውህደት የሚከተሉትን ይጠይቃል፡-**

**(i) እንደነዚህ ያሉትን ተጽዕኖዎች የመፍታት ኀላፊነትን በንግድ ድርጅቱ ውስጥ አግባብነት ላለው ደረጃ እና ተግባር መመደብ፤**

**(ii) የውስጥ ውሳኔ አሰጣጥ፣ የበጀት ድልድል እና የቁጥጥር ሂደቶች ለእንደዚህ ዓይነት ተጽዕኖዎች ውጤታማ ምላሾችን ለመስጠት ማስቻል፡፡**

**(ለ) ተገቢው እርምጃ በሚከተለው መሠረት ይለያያል፡-**

**(i) የንግድ ድርጅቱ አሉታዊ ተጽዕኖ ያደረሰ ወይም ለተጽዕኖው አስተዋጽዖ ያበረከተ መሆኑ፣ ወይም የተሳተፈበት ብቸኛ ምክንያት ተጽዕኖው በቀጥታ ከሥራው፣ ከምርቶቹ ወይም ከአገልግሎቶቹ ጋር በቀጥታ በተያያዘ የንግድ ግንኙነት መሆኑ፤**

**(ii) የሚያስከትለውን ጉዳት ለመፍታት ያለው ዐቅም፡፡**

***ማብራሪያ***

*በሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖ ግምገማ የተገኙ ዝርዝር ግኝቶች የጎንዮሽ ውህደት በንግድ ድርጅቱ ሁሉም ተግባራት ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የንግድ ድርጅቱ የሰብአዊ መብቶች ፖሊሲ ቁርጠኝነት በሁሉም አግባብነት ባላቸው የንግድ ተግባራቱ ውስጥ ሲካተቱ ብቻ ነው፡፡ ይህ የሚፈለገው የግምገማ ግኝቶቹን በትክክል በመገንዘብ፣ ተገቢውን ክብደት እንዲያገኙ እና እንዲተገበሩ ለማድረግ ነው፡፡*

*የንግድ ተቋማት የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን በሚገመግሙበት ጊዜ ሁለቱንም ተጨባጭ እና ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ማየት ይኖርባቸዋል፡፡ በንግድ ተቋሙ ውስጥ ባሉ የግኝቶች የጎንዮሽ ውህደት አማካኝነት ሊከሰቱ የሚችሉ ተጽዕኖዎችን መከላከል ወይም መቀነስ አለባቸው፤ ተጨባጭ ተጽዕኖዎች እንዲሁም አስቀድመው የተከሰቱትን ደግሞ የመፍትሔ ርዕሰ ጉዳይ መሆን አለባቸው (መርሕ 22)፡፡*

*አንድ የንግድ ድርጅት በሰብአዊ መብቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚያመጣበት ወይም በሚያስከትልበት ጊዜ ተጽዕኖውን ለማቆም ወይም ለመከላከል አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡*

አንድ የንግድ ድርጅት ለሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖ አስተዋጽዖ ሲያደርግ ወይም አስተዋጽዖ ሊያደርግ በሚችልበት ጊዜ አስተዋጽዖውን ለማቆም ወይም ለመከላከል አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ እና የቀረውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ያለውን ዐቅም መጠቀም አለበት። ድርጅቱ ጉዳት በሚያስከትል አካል የተሳሳቱ ድርጊቶች ላይ ለውጥ የማምጣት ችሎታ ሲኖረው ዐቅም እንዳለው ይቆጠራል።

አንድ የንግድ ድርጅት ለሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖ አስተዋጽዖ ያላበረከተ እንደሆነ ፣ ነገር ግን ተጽዕኖው ከሌላ አካል ጋር ካለው ከሥራው፣ ከምርቶቹ ወይም ከአገልግሎቶቹ ጋር በቀጥታ የተገናኘ የንግድ ግንኙነት እንደሆነ ሁኔታው ይበልጥ የተወሳሰበ ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ተገቢውን እርምጃ ለመወሰን ከሚያስፈልጉት ምክንያቶች መካከል ድርጅቱ በሚመለከተው አካል ላይ ያለው ዐቅም፣ ግንኙነቱ ለድርጅቱ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ፣ የተፈጸመው ጥሰት ክብደት እና ከድርጅቱ ጋር ያለውን ግንኙነት ማቋረጥ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ውጤቶችን ሊያስከትል የሚችል መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል።

ሁኔታው እና በሰብአዊ መብቶች ላይ ያለው አንድምታ በተወሳሰበ ቁጥር ድርጅቱ እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለበት ለመወሰን ከገለልተኛ ባለሙያ ምክር የማግኘቱ አስፈላጊነት ይበልጥ እየጠነከረ ይሄዳል።

የንግድ ድርጅቱ አሉታዊ ተጽዕኖውን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ የሚያስችል ዐቅም ያለው እንደሆነ ሊጠቀምበት ይገባል። ዐቅም ከሌለው ወይም የሚያንሰው እንደሆነ ዐቅሙን የሚጨምርባቸው መንገዶች ይኖራሉ። ለምሳሌ የዐቅም ግንባታ ወይም ሌሎች ማበረታቻዎችን ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ወይም ከሌሎች በግል ተቋማት (ተሳታፊዎች) ጋር በመተባበር ዐቅሙን ሊጨምር ይችላል።

አንድ ድርጅት አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ የሚያስችል ዐቅም የሌለው እና ዐቅሙንም መጨመር የማይችልባቸው ሁኔታዎች አሉ። እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ ድርጅቱ ግንኙነቱን ቢያቆም ሊከተሉ የሚችሉ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን በተመለከተ ተአማኒነት ያላቸውን ግምገማዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ግንኙነቱን ለማቆም ማሰብ ይኖርበታል። ግንኙነቱ ለድርጅቱ "ወሳኝ" ሲሆን ግንኙነቱን ማቆም ተጨማሪ ፈተናዎችን ወይም ተግዳሮቶች ያስነሳል/ይፈጥራል። አንድ ግንኙነት ለድርጅቱ ንግድ አስፈላጊ የሆነ ምርት ወይም አገልግሎት የሚያቀርብ ከሆነ እና ምንም ምክንያታዊ የምንጭ አማራጭ ከሌለ እንደ ወሳኝ ግንኙነት ሊቆጠር ይችላል። እዚህ ላይ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖው አስከፊነት ግምት

ውስጥ መግባት አለበት፤ ጥሰት እየጠነከረ በሄደ ቁጥር ድርጅቱ ግንኙነቱን ማቆም እንዳለበት ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት በፍጥነት ለውጥ ማየት ያስፈልገዋል። ያም ሆነ ይህ፣ ጥሰቱ እስከቀጠለ ድረስ እና ድርጅቱ በግንኙነቱ ውስጥ እስካለ ድረስ ተጽዕኖውን ለመቅረፍ የራሱን ቀጣይ ጥረቶችን ማሳየት እና ቀጣይነት ያለው ግንኙነቱ የሚያስከትለውን ውጤት ከመልካም ሥም፣ ከገንዘብ ወይም ከሕግ አንጻር ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለበት።

**20. አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች እየተፈቱ መሆኑን ለማረጋገጥ የንግድ ድርጅቶች የምላሻቸውን ውጤታማነት መከታተል አለባቸው።**

**ክትትል፡-**

**(ሀ) በተገቢው ገላጭ እና አሃዛዊ አመልካቾች ላይ የተመሠረተ መሆን፤**

**(ለ) የተጎዱ ባለድርሻ አካላትን ጨምሮ ከውስጥ እና ከውጭ ምንጮች የተሰጡ ግብረ መልሶችን የሚጠቀም መሆን አለበት።**

***ማብራሪያ***

*ለንግድ ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ፖሊሲዎቹ በጥሩ ሁኔታ እየተተገበሩ መሆናቸውን፣ ለተለዩት የሰብአዊ መብት ተጽዕኖዎች ውጤታማ ምላሽ መስጠቱን ለማወቅ እና ቀጣይነት ያለው መሻሻል እንዲኖር ለማድረግ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው።*

*የንግድ ድርጅቶች ለጉዳት ወይም የመገለል አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖች ወይም ሕዝቦች አካል በሆኑ ግለሰቦች ላይ ለሚደርሱ ተጽዕኖዎች የሚሰጡትን ምላሽ ውጤታማነት ለመከታተል ልዩ ጥረት ማድረግ አለባቸው።*

*ክትትል በተገቢ ሪፖርት/ዘገባ አቀራረብ ሂደቶች መካተት አለበት። የንግድ ድርጅቶች ከሌሎች ጉዳዮች ጋር በተያያዘ አስቀድመው የሚጠቀሙባቸውን ሥልቶች ሊጠቀሙ ይችላሉ። ይህም እንደ አስፈላጊነቱ የአፈጻጸም ውሎችን እና ግምገማዎችን እንዲሁም የዳሰሳ ጥናቶችን እና ኦዲቶችን፣ በጾታ የተከፋፈለ መረጃን ሊያካትት ይችላል። የአሠራር ደረጃ የቅሬታ አቀራረብ ሥልት በቀጥታ ከተጎዱት ሰዎች ስለንግድ ድርጅቱ የሰብአዊ መብቶች ትጋት ውጤታማነት ጠቃሚ ግብረ መልስ ሊያስገኝ ይችላል (መርሕ 29 ይመልከቱ)።*

**21. የንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኗቸውን እንዴት እንደሚፈቱ ለማሳየት፣ በተለይም በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ወይም በተወካዮች**

**ሥጋቶች ሲነሱ ከድርጅታቸው ውጪ ላሉ አካላት ይህንን ለማሳወቅ መዘጋጀት አለባቸው። ሥራቸው ወይም የሥራ ሁኔታቸው የሰብአዊ መብቶች ላይ ከባድ ተጽዕኖዎችን የሚፈጥሩ ድርጅቶች እንዴት ተጽዕኖዎቹን እንደሚፈቱ በመደበኛነት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። በሁሉም ሁኔታዎች፣ የማሳወቅ ሥራዎች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፤**

**(ሀ) የድርጅቱን የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን የሚያንፀባርቅ እና ለታለመላቸው ታዳሚዎች ተደራሽ በሆነ ቅርጽ እና ድግግሞሽ መሆን አለበት፤**

**(ለ) ለተፈጠረው የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖ የድርጅቱ ምላሽ በቂ መሆኑን ለመገምገም የሚያስችል በቂ የሆነ መረጃ መስጠት፤**

**(ሐ) በምላሹ በተጎዱ ባለድርሻዎች፣ ሠራተኞች ወይም ሕጋዊ የንግድ ምስጢራዊነት መስፈርቶች ላይ አደጋዎችን አለማስከተል።**

**በሁሉም ሁኔታዎች፣ ግንኙነቶች የኢንተርፕራይዝ የሰብአዊ መብት ተፅእኖዎችን የሚያንፀባርቁ እና ለታለመላቸው ታዳሚዎች ተደራሽ የሚሆኑ ቅርጾች እና ድግግሞሽ መሆን አለባቸው።**

**ማብራሪያ**

ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነት የንግድ ድርጅቶች በእርግጥ ሰብአዊ መብቶችን እንደሚያከብሩ ለማወቅም ለማሳየትም የሚያስችሏቸው ፖሊሲዎች እና ሂደቶች እንዲኖሯቸው ይጠይቃል። ማሳየት፦ ግንኙነትን፣ ተጽዕኖ ሊደርስባቸው ለሚችሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እንዲሁም ባለሀብቶችን ጨምሮ ለሌሎች ባለድርሻ አካላት፣ የግልጽነት እና ተጠያቂነት አካሄዶችን ማቅረብን ያካትታል።

ግንኙነት፤ የአካል ስብሰባዎችን፣ በበየነ መረብ ውይይት ማድረግን፣ ጉዳት ከደረሰባቸው ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ምክክርን እና መደበኛ ይፋዊ ሪፖርትን ጨምሮ የተለያዩ ዓይነት ቅርፆችን ሊወስድ ይችላል። መደበኛ ሪፖርት፣ ከተለመዱ ዓመታዊ ሪፖርቶች እና የድርጅት ኀላፊነት/ ዘለቄታዊነት ሪፖርቶች ወደ በይነ መረብ ወቅታዊ የማድረግ /update/ እና የተዋቀሩ የፋይናንስና የፋይናንስ ያልሆኑ ሪፖርቶችን ማካተት በሂደት እየተሻሻለ ነው።

ከንግድ እንቅስቃሴዎች ባሕሪም ይሁን አሠራር ከባድ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሥጋት በሚኖር ጊዜ ከንግድ ድርጅቶች መደበኛ ሪፖርት ይጠበቃል። ሪፖርቱ ድርጅቶቹ በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተጽዕኖ የሚለዩበትን እና የሚያስተካክሉበትን መንገድ የተመለከቱ ርዕስ ጉዳዮችንና

ጠቋሚዎችን ሊሸፍን ይገባል። የሰብአዊ መብቶች ሪፖርትን በገለልተኛ አካል ማረጋገጥ ይዘቱንና ተአማኒነቱን ሊያጠናክር ይችላል። ዘርፍ-ተኮር ጠቋሚዎች ደግሞ ተጨማሪ ጠቃሚ ዝርዝር ለማቅረብ ይረዳሉ።

***መፍትሔ ስለመስጠት***

**22. *የንግድ ድርጅቶች አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳስከተሉ ወይም ለአሉታዊ ተጽዕኖ አስተዋጽዖ እንዳደረጉ በሚያውቁበት ጊዜ ቅቡልነት ባላቸው ሂደቶች አማካኝነት መፍትሔ ማቅረብ ወይም ትብብር ማድረግ አለባቸው።***

***ማብራሪያ***

አንድ የንግድ ድርጅት ከሁሉ የተሻሉ ፖሊሲዎችና ልማዶች ቢኖሩትም እንኳ አስቀድሞ ያልጠበቀውን ወይም ሊከላከለው ያልቻለውን የሰብአዊ መብቶች ጉዳት ሊያስከትል ወይም ለመከሰቱ አስተዋጽዖ ሊያበረክት ይችላል።

አንድ የንግድ ድርጅት እንዲህ ያለውን ሁኔታ በሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት ሂደትም ሆነ በሌሎች መንገዶች ለይቶ በሚያውቅበት ጊዜ የሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነት በራሱ ወይም ከሌሎች በግል ተቋማት (ተሳታፊዎች) ጋር በመተባበር መፍትሔ ለመስጠት ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ይጠይቃል። በንግድ ድርጅቶች እንቅስቃሴዎች ተጽዕኖ ሊደርስባቸው ለሚችሉ አካላት የአሠራር ደረጃ የቅሬታ ስልት በመርሕ 31 ላይ እንደተገለጸው የተወሰኑ ዋና መስፈርቶች ሲሟሉ መፍትሔ መስጠትን ለማስቻል አንዱ ውጤታማ ስልት ሊሆን ይችላል።

የንግድ ድርጅቱ ያላደረሳቸው ወይም አስተዋጽዖ ያላበረከተባቸው ነገር ግን ከሥራው፣ ከምርቶቹ ወይም ከአገልግሎቶቹ ጋር በቀጥታ የተገናኙ አሉታዊ ተጽዕኖዎች ከተከሰቱ፣ ምንም እንኳ ሚና ቢኖረውም የሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነት ድርጅቱ ራሱ ለችግሩ መፍትሔ እንዲሰጥ አይጠይቅም። አንዳንድ ሁኔታዎች በተለይም ወንጀል ተፈጽሟል ሲባል ከፍርድ አሠራር ጋር መተባበርን ይጠይቃሉ።

ስለመፍትሔ ተደራሽነት በተመለከተ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች ውንጀላዎች ክርክርን ጨምሮ መፍትሔ የሚፈለግባቸው ስልቶች ላይ ተጨማሪ መንገዶች በምዕራፍ 3 ውስጥ ተካተዋል።

***የዐውድ ጉዳዮች***

**23. *በሁሉም ሁኔታዎች የንግድ ድርጅቶች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው:***

*ሀ) በሚሠሩበት ቦታ ሁሉ ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጎች ማክበር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያላቸውን ሰብአዊ መብቶችን ማክበር፤*

*(ለ) እርስ በርስ የሚጋጩ መስፈርቶች ሲያጋጥሙ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ የሰብአዊ መብቶች መርሖችን ለማክበር መንገዶችን መፈለግ፤*

*(ሐ) በሚሠሩበት ቦታ ሁሉ ለከባድ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መንስዔ የመሆን ወይም አስተዋጽዖ የማድረግን ሥጋት እንደ ሕጋዊ ተገዢነት ጉዳይ መመልከት::*

*ማብራሪያ*

*ምንም እንኳን የተለዩ ሀገራዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታዎች የድርጅቶች እንቅስቃሴዎች እና የንግድ ግንኙነቶች የሰብአዊ መብቶች ሥጋቶች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ቢችሉም፣ ሁሉም የንግድ ድርጅቶች በሚንቀሳቀሱበት ቦታ ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ተመሳሳይ ኀላፊነት አለባቸው:: የሀገር ውስጥ ዐውድ ይህንን ኀላፊነት ሙሉ በሙሉ መወጣትን የማይቻል በሚያደርገው ጊዜ፣ ንግድ ድርጅቶች በሁኔታዎቹ ውስጥ በተቻለ መጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያላቸውን የሰብአዊ መብቶች መርሖች ማክበር እና በዚህ ረገድ ጥረታቸውን ለማሳየት መቻል ይጠበቅባቸዋል::*

*አንዳንድ የሥራ አካባቢዎች፣ ለምሳሌ በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች፣ ድርጅቶች በሌሎች በግል ተቋማት (ተሳታፊዎች) ለሚፈጸሙ ከባድ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች (ለምሳሌ በጸጥታ ኃይሎች) ተባባሪ በመሆን ሥጋትን ሊጨምሩ ይችላሉ:: ከድንበር ተሻጋሪ የፍትሐብሔር ክሶች የመነጨ የድርጅቶች ሕጋዊ ተጠያቂነት እየሰፋ ከመሆኑ እና የንግድ ድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነትን በሚያስቀምጡ/ዕውቅና በሚሰጡ ግዛቶች የዓለም አቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤትን የሚያቋቁመው የሮም ስምምነት ድንጋጌዎች ከመካተታቸው አንጻር የንግድ ድርጅቶች ይህንን ሥጋት እንደ የሕግ ተገዢነት ጉዳይ አድርገው ሊመለከቱት ይገባል::*

*በተጨማሪም፣ የድርጅት ዳይሬክተሮች፣ ኀላፊዎች እና ሠራተኞች ከባድ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ለሚያደርሱ ድርጊቶች በግለሰብ ደረጃ ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ::*

*እንደነዚህ ባሉ ውስብስብ ሁኔታዎች ውስጥ የንግድ ድርጅቶች ሁኔታውን እንደማያባብሱ ማረጋገጥ አለባቸው:: እንዴት የተሻለ ምላሽ እንደሚሰጡ ሲገመግሙ፣ ከድርጅቱ ባለሙያዎች እና የውስጥ ሁለገብ ምክክር ባሻገር*

ከውጪ፣ ተዓማኒ እና ገለልተኛ ባለሙያዎችን፣ ከመንግሥታት፣ ከሲቪል ማኅበረሰብ፣ ከብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና ከሚመለከታቸው የብዙኃን ባለድርሻ አካላት ተግባራት ጋር እንዲማከሩ ይመከራሉ፡፡

**24. ተጨባጭ እና ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን ለመቅረፍ ለድርጊቶች ቅድሚያ መስጠት በሚያስፈልግበት ጊዜ የንግድ ድርጅቶች በጣም ከባድ የሆኑትን ወይም በዘገየ ምላሽ ሊታረሙ የማይችሉትን መጀመሪያ ለመከላከል እና ለማቃለል መጣር አለባቸው፡፡**

***ማብራሪያ***

የንግድ ድርጅቶች ሁሉንም አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች መፍታት የሚገባቸው ቢሆንም፣ ሁሉንም በተመሳሳይ ጊዜ መፍታት ሁልጊዜ የማይቻል ሊሆን ይችላል፡፡ የተለየ የሕግ መመሪያ ከሌለና ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን የንግድ ድርጅቶች የዘገየ ምላሽ የመልሶ ማቋቋም ሥራን እንደሚጎዳ በመገንዘብ በጣም ከባድ ከሆኑት የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች መጀመር አለባቸው፡፡ ክብደት በዚህ ዐውድ ውስጥ ፍፁም ጽንሰ ሐሳብ አይደለም፣ ነገር ግን የንግድ ድርጅቱ ከለያቸው ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎች አንፃር የሚታይ ነው፡፡

# III. የመፍትሔ ተደራሽነት

## *ሀ. መሠረታዊ መርሕ*

**25. ከንግድ ነክ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የመጠበቅ ግዴታ አካል እንደመሆኑ መጠን በግዛታቸው እና/ወይም በሥልጣናቸው ውስጥ እንደዚህ ዓይነት በደል ሲደርስ፤ በእነዚህ ጥሰቶች የተጎዱ አካላት ውጤታማ መፍትሔ እንደሚያገኙ ለማረጋገጥ ሀገራት በፍትሕ፣ በአስተዳደራዊ፣ በሕግ ወይም በሌሎች ተገቢ መንገዶች ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡**

***ማብራሪያ***

ከንግድ ጋር የተያያዙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሲፈጸሙ መንግሥታት ለመመርመር፣ ለመቅጣት እና ለማስተካከል ተገቢውን እርምጃ ካልወሰዱ

በስተቀር የመንግሥት የመጠበቅ ግዴታ ደካማ ወይም ትርጉም የለሽ ሊሆን ይችላል።

ውጤታማ መፍትሔ ማግኘት የሥርዓት እና ተጨባጭ ገጽታዎች አሉት። በአጠቃላይ ዓላማቸው የተከሰቱትን የሰብአዊ መብቶች ጥፋቶችን ለመከላከል ወይም ለማስተካከል የሆኑ በዚህ ክፍል ውስጥ በተገለጹት የቅሬታ ማቅረቢያ ስልቶች የሚቀርቡት መፍትሔዎች የተለያዩ ተጨባጭ ቅርጾችን ሊወስዱ ይችላሉ። መፍትሔ ይቅርታ መጠየቅን፣ ማካካሻን፣ ማገገሚያን፣ የገንዘብ ወይም ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ካሳዎችን እና የቅጣት እቀባዎችን (የወንጀልም ሆነ አስተዳደራዊ፣ እንደ የገንዘብ ቅጣቶች) እንዲሁም እንደ እገዳ ወይም እንዳይደግም ዋስትና መስጠት ዓይነት እርምጃዎችን በመውሰድ ጉዳትን መከላከልን ሊያካትት ይችላል። የመፍትሔ አቅርቦት ሂደቶች ገለልተኛ፣ ከሙስና የተጠበቁ እና በውጤቱ ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ የፖለቲካ ወይም ሌሎች ሙከራዎች የፀዱ መሆን አለባቸው።

ለእነዚህ የመመሪያ መርሖች ሲባል ቅሬታ ማለት በሕግ፣ በውል፣ በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ የተስፋ ቃል፣ በልማዳዊ አሠራር፣ ወይም በተጎዱ ማኅበረሰቦች ፍትሐዊነት አጠቃላይ እሳቤዎች ላይ የተመሠረተ የግለሰብን ወይም የቡድንን የመብት ስሜት የሚቀሰቅስ የፍትሕ መጓደል እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። የቅሬታ ስልት የሚለው ቃል ከንግድ ነክ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ጋር በተያያዘ ቅሬታ የሚነሳበት እና መፍትሔ የሚፈለግበትን ማንኛውንም መደበኛ፣ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ፣ ከፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ዳኝነት ውጪ የሆነ ሂደትን ለማመልከት ይጠቅማል።

መንግሥታዊ የቅሬታ ስልቶች በመንግሥት ቅርንጫፍ ወይም ወኪል ወይም በገለልተኛ አካል በሕግ ወይም በሕገ መንግሥታዊ መሠረት ሊከናወኑ የሚችሉ ናቸው። እነዚህም ከፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ዳኝነት ውጪ ሊሆኑ ይችላሉ። በአንዳንድ ስልቶች ተጎጂዎች መፍትሔ በመፈለግ ላይ በቀጥታ የሚሳተፉ ሲሆን፤ በሌሎች ደግሞ ሦስተኛ ወገን እነርሱን ወክሎ መፍትሔ ይፈልጋል። ለአብነት ያህል ፍርድ ቤቶች (በወንጀልም ሆነ በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች)፣ የሠራተኛ ፍርድ ቤቶች፣ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት፣ የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ድርጅት ሁለገብ ድርጅቶች በመመሪያው ሥር ብሔራዊ የግንኙነት ነጥቦች (National Contact Points under the Guidelines for Multinational Enterprises of the Organisation for Economic Co-operation and Development)፣

በርካታ እንባ ጠባቂ መሥሪያ ቤቶች እና በመንግሥት ተቋማት ሥራ ያሉ የቅሬታ መስተንግዶ ሥርዓቶች ይገኙበታል፡፡

ለንግድ ነክ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች መፍትሔ ማግኘትን ማረጋገጥ መንግሥታት ስለነዚህ ስልቶች የሕዝብ ግንዛቤ ማሳደግ፣ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ማሳወቅ እና ይህን ለማድረግ ማንኛውንም ድጋፍ (ገንዘብ ነክ ወይም የባለሙያ) ማመቻቸትን ይጠይቃል፡፡

መንግሥታዊ ከፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ዳኝነት ውጪ ያሉ የቅሬታ ስልቶች ለሰፊው የመፍትሔ ሥርዓት መሠረት ሊሆኑ ይገባል፡፡ እንዲህ ባለው ሥርዓት ውስጥ የአሠራር ደረጃ የቅሬታ ዘዴዎች ቀደምት/የመጀመሪያ ደረጃ ምላሽ እና መፍትሔን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ መንግሥታዊ እና የአሠራር ደረጃ ስልቶች ደግሞ በትብብር ተነሳሽነት የማሻሻያ ተግባራት፤ እንዲሁም በዓለም አቀፍ እና በአህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ዘዴዎች ሊሟሉ ወይም ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ዘዴዎች በተመለከተ ተጨማሪ መመሪያ ከመመሪያ መርሖች 26 እስከ 31 ቀርቧል፡፡

**ለ. የአሠራር መርሖች**

**በፍርድ ቤት የሚሰጡ መንግሥታዊ የዳኝነት ስልቶች**

26. **ከንግድ ጋር የተያያዙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመፍታት መንግሥታት የሀገር ውስጥ የፍርድ ቤት የዳኝነት ስልቶችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ መፍትሔ ማግኘትን ሊከለክሉ የሚችሉ የሕግ፣ የተግባር እና ሌሎች ተዛማጅ እንቅፋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ መንገዶችን ግምት ውስጥ ማስገባትን ጨምሮ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡**

**ማብራሪያ**

ውጤታማ የፍርድ ቤት ዳኝነት ስልቶች የመፍትሔ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የእነዚህ ስልቶች ንግድ ነክ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን የመፍታት ዐቅማቸው በገለልተኛነታቸው፣ በታማኝነታቸው እና ፍትሐዊ ሂደታቸውን በመፈጸም ችሎታቸው ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የፍትሕ ሂደት መፍትሔ ለማግኘት አስፈላጊ በሚሆንበት ሁኔታ ወይም ውጤታማ የመፍትሔ አማራጭ ምንጮች በማይገኙበት ጊዜ ሀገራት ሕጋዊ የሆኑ ጉዳዮች ለፍርድ ቤት እንዳይቀርቡ የሚከለክሉ እንቅፋቶች እንዳይፈጠሩ በማድረግ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ እንዲሁም ሀገራት የፍትሕ አቅርቦት በፍትሕ ሂደቱ ውስጥ ባለ ሙስና እንዳይከለከል፣ ፍርድ ቤቶች ከሌሎች የመንግሥት ተወካዮች እና ከንግድ አካላት ከሚደርስባቸው ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጫናዎች ነጻ መሆናቸውን፣ እና የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕጋዊ እና ሰላማዊ እንቅስቃሴዎች እንዳይደናቀፉ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

ከንግድ ነክ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ጋር የተያያዙ ሕጋዊ ጉዳዮች መፍትሔ እንዳይሰጡ የሚከለክሉ የሕግ እንቅፋቶች ሊኖሩ የሚችሉ ሲሆን፣ ይህም የሚሆነው ለምሳሌ፦

- በሀገር ውስጥ የወንጀል እና የፍትሐ ብሔር ሕጎች በድርጅት ቡድን አባላት መካከል ሕጋዊ ኀላፊነት የሚወሰድበት መንገድ ተገቢውን ተጠያቂነት ለማስወገድ የሚያመቻች ከሆነ፤
- አመልካቾች ባሉበት ሀገር የፍትሕ መነፈግ በሚያጋጥማቸው ጊዜ እና ጥያቄያቸው ምንም ይሁን ምን የሀገራቸውን ፍርድ ቤቶች ማግኘት የማይችሉ ከሆነ፤
- እንደ ቀደምት ሕዝቦች እና ስደተኞች ያሉ የተወሰኑ ቡድኖች ለሰፊው ሕዝብ የሚሰጠውን ሕጋዊ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ በተመሳሳይ ደረጃ እንዳያገኙ የሚገለሉ ከሆነ፤ ነው፡፡

የፍትሕ መፍትሔዎች ተደራሽ እንዳይሆኑ የሚያደርጉ የተግባር እና የሥርዓት እንቅፋቶች ሊኖሩ የሚችሉ ሲሆን፣ ይህም የሚሆነው ለምሳሌ፦

- አመልካቾች አቤቱታቸውን ለማቅረብ የሚጠየቁ ወጪዎች ተገቢ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያለው እንቅፋት ከመሆን ባለፈ እና/ወይም በመንግሥት ድጋፍ፣ በገበያ ላይ የተመሠረቱ ስልቶች (እንደ ሙግት መድን እና ሕጋዊ ክፍያ መዋቅሮች) ወይም ሌሎች መንገዶች ወደ ምክንያታዊ ደረጃዎች ሊቀንስ የማይችል ከሆነ፤

- የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢዎች በሀብት እጥረት ምክንያት ወይም ለሕግ ጠበቃዎች የተመቻቹ ሌሎች ማበረታቻዎች ባለመኖራቸው ምክንያት የይገባኛል ጠያቂዎች የሕግ ውክልና ለማግኘት የሚቸገሩ ከሆነ፤
- የይገባኛል ጥያቄዎችን ለማጠቃለል ወይም የውክልና ክስ ሂደቶችን (እንደ የቡድን ክስ እና ሌሎች የጋራ ክስ ማቅረቢያ ሥርዓቶች) ለማከናወን የሚያስችሉ በቂ አማራጮች ከሌሉ፣ እና ይህ የግለሰብ ጠያቂዎችን ውጤታማ መፍትሔ ማግኘት የሚከለክል ከሆነ፤
- ዐቃቤ ሕግ ከሰብአዊ መብቶች ጋር በተያያዙ ወንጀሎች ውስጥ የግለሰብ እና የንግድ ተሳትፎን የመመርመር የመንግሥት ግዴታን ለማሟላት በቂ ሀብት፣ ዕውቀት እና ድጋፍ የሌለው ከሆነ፤ ነው::

አብዛኛዎቹ እነዚህ እንቅፋቶች ከንግድ ነክ የሰብአዊ መብቶች አቤቱታዎች ጋር በተያያዘ በተከራካሪ ወገኖች መካከል ያለው የገንዘብ፣ የመረጃ ተደራሽነት እና ዕውቀት በተደጋጋሚ አለመመጣጠን የተፈጠሩ ወይም የተባባሱ ናቸው:: በተጨማሪም፣ በግልጽ አድልዎ ወይም የዳኝነት ሥርዓቱ የተነደፈበት እና የሚሠራበት መንገድ ባስከተለው ያልተፈለገ ውጤት ምክንያት ከፍተኛ የተጋላጭነት ወይም የመገለል ሥጋት ውስጥ ያሉ ቡድኖች ወይም ሕዝቦች ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች እነዚህን ስልቶች (የዳኝነት ሥርዓት) ለማግኘት፣ ለመጠቀም እና ተጠቃሚ ለመሆን ብዙ ጊዜ ተጨማሪ የባህል፣ የማኅበራዊ፣ የአካል እና የፋይናንስ እንቅፋቶች ያጋጥማቸዋል:: በእያንዳንዱ የመፍትሔው ሂደት፣ ማለትም ተደራሽነት፣ ሂደት እና ውጤት ላይ ለእነዚህ ዓይነት ቡድኖች ወይም ሕዝቦች መብቶች እና ልዩ ፍላጎቶች ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል::

## ከፍርድ ቤት ውጪ ያሉ መንግሥታዊ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች

27. ***ሀገራት ንግድ ነክ የሰብአዊ መብቶች ጥሰትን ለመፍታት ከፍርድ ቤት የቅሬታ መፍቻ ስልቶች ጎን ለጎን ውጤታማ እና ተገቢ የሆኑ ከፍርድ ቤት ውጪ ያሉ መንግሥታዊ የቅሬታ መፍቻ ስልቶችን እንደ አጠቃላይ የመንግሥታዊ የቅሬታ መፍቻ ሥርዓት አካል አድርገው ማቅረብ አለባቸው::***

***ማብራሪያ***

አስተዳደራዊ፣ የሕግ እና ሌሎች ከፍርድ ቤት ውጪ ያሉ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች የፍርድ ቤት የቅሬታ መፍቻ ስልቶችን በመደገፍ እና በማሟላት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የፍርድ ቤት ሥርዓቱ ውጤታማ እና በቂ ሀብት ያለው ቢሆንም ሁሉንም የመብት ጥሰቶች የመፍታት ኀላፊነት ሊሸከሙ አይችሉም፤ የፍርድ ቤት መፍትሔም ሁልጊዜ አስፈላጊ አይደለም፣ ወይም ሁልጊዜ ለሁሉም የይገባኛል ጠያቂዎች ተመራጭ አካሄድ አይደለም፡፡

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከፍርድ ቤት ውጪ ያሉ የቅሬታ መፍቻ ስልቶችን ሥልጣናቸውን በማስፋት እና/ወይም አዳዲስ ስልቶችን በመጨመር ከንግድ ጋር በተያያዙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች መፍትሔ አሰጣጥ ላይ ያሉ ክፍተቶችን መሙላት ይቻላል፡፡ በሚመለከታቸው ጉዳዮች፣ በሚመለከታቸው ማናቸውም የሕዝብ ጥቅሞች እና በተከራካሪ ወገኖች ፍላጎት ላይ በመመሥረት እነዚህ በሽምግልና ላይ የተመሠረቱ፣ ዳኝነት የሚሰጡ ወይም ሌሎች ለባህል ተስማሚ እና ከመብቶች ጋር የሚጣጣሙ ሂደቶችን የሚከተሉ ወይም ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን የሚያካትቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የእነዚህ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ በመርሕ 31 ላይ የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላት አለባቸው፡፡

በዚህ ረገድ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት በተለየ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡

እንደ የፍርድ ቤት የቅሬታ መፍቻ ስልቶች ሁሉ፣ ሀገራት ከንግድ ነክ የሰብአዊ መብቶች ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚፈጠሩ አለመመጣጠኖችን እና ከፍተኛ የተጋላጭነት ወይም የመገለል ሥጋት ውስጥ ያሉ ቡድኖች ወይም ሕዝቦች ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች ስልቶችን ለመጠቀም የሚያጋጥሟቸውን ተጨማሪ እንቅፋቶችን ለመፍታት መንገዶችን ማጤን አለባቸው፡፡

***መንግሥታዊ ያልሆኑ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች***

28. ***ሀገራት ከንግድ ነክ የሰብአዊ መብቶች ጉዳቶች ጋር በተገናኘ ውጤታማ መንግሥታዊ ያልሆኑ የቅሬታ መፍቻ ስልቶችን ለማግኘት የሚያስችሉ መንገዶችን ማመቻቸት አለባቸው፡፡***

*ማብራሪያ*

*መንግሥታዊ ካልሆኑ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች ውስጥ አንዱ ምድብ በአንድ የንግድ ድርጅት ብቻ ወይም ከባለድርሻ አካላት ጋር፣ በኢንዱስትሪ ማኅበር ወይም በብዙ ባለድርሻ አካላት የሚተዳደሩትን ያጠቃልላል። እነዚህ ከፍርድ ቤት ውጪ የሆኑ የቅሬታ መፍቻዎች ቢሆኑም ዳኝነትን፣ ውይይትን መሠረት ያደረጉ፣ ወይም ሌላ ከባህል ጋር የሚስማሙ እና ከመብት ጋር የሚጣጣሙ ሂደቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። እነዚህ ስልቶች እንደ በቀላሉ ተደራሽነት እና አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት፣ ወጪዎችን መቀነስ እና/ወይም ድንበር ተሻጋሪ ተደራሽነት ያሉ ልዩ ጥቅሞችን ሊሰጡ ይችላሉ።*

*ሌላው ምድብ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች አካላትን ያጠቃልላል። እነዚህ ብዙ ጊዜ ሀገራት የሰብአዊ መብቶችን የማክበር ግዴታቸውን ጥሰዋል በሚባልበት ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። ይሁን እንጂ አንዳንዴ ደግሞ የንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በሚያደርሱበት ጊዜ ሀገራት የመጠበቅ ግዴታቸውን ሳይወጡ በመቅረታቸው ጥቅም ላይ ይውላሉ።*

*ሀገራት እራሳቸው ከሚያቀርቧቸው ስልቶች ጎን ለጎን እንደ እነዚህ ዓይነት አማራጮች ዙሪያ ግንዛቤን በማሳደግ ወይም በሌላ መንገድ ተደራሽነታቸውን በማመቻቸት ረገድ አጋዥ ሚና መጫወት ይችላሉ።*

29. ***የንግድ ድርጅቶች አሉታዊ ተጽዕኖ ለደረሰባቸው ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች ውጤታማ የሆነ የአሠራር ደረጃ የቅሬታ መፍቻ ስልቶችን በማቋቋም ወይም በመሳተፍ ቅሬታዎች ቶሎ እንዲፈቱ እና በቀጥታ መፍትሔ እንዲያገኙ ማስቻል አለባቸው።***

*ማብራሪያ*

*የአሠራር ደረጃ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች በንግድ ድርጅት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊደርስባቸው ለሚችሉ ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች በቀጥታ ተደራሽ ናቸው። እነዚህ በተለምዶ የሚተዳደሩት በድርጅቶች በራሳቸው ብቻ ወይም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን ጨምሮ ከሌሎች ጋር በመተባበር ነው። እንዲሁም በጋራ ተቀባይነት ላለው የውጪ ባለሙያ ወይም አካል ሊሰጡ ይችላሉ። ቅሬታ አቅራቢዎች ቅሬታቸውን ወደ እነዚህ የቅሪታ መፍቻ*

ስልቶች ከማቅረባቸው በፊት ሌሎችን የቅሬታ መፍቻ ስልቶች እንዲጠቀሙ አይጠየቁም:: ጉዳዮችን ለመገምገም እና ማንኛውንም ጉዳት ለማስተካከል/መፍትሔ ለመፈለግ የንግድ ድርጅቱን በቀጥታ ማሳተፍ ይችላሉ::

የአሠራር ደረጃ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች የንግድ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኀላፊነትን በተመለከተ ሁለት ቁልፍ ተግባራትን ያከናውናሉ::

- አንደኛ፣ የአንድ ድርጅት ቀጣይነት ያለው የሰብአዊ መብቶች ተገቢ ትጋት (human rights due diligence) አካል ሆኖ አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን መለየትን ይደግፋሉ:: ይህን የሚያደርጉት በድርጅቱ ተግባሮች በቀጥታ አሉታዊ ተጽዕኖ እየደረሰባቸው እንደሆነ ወይም እንደሚደርስባቸው በሚያምኑበት ጊዜ ሥጋታቸውን ለማንሳት የሚያስችል ሥርዓት በማመቻቸት ነው:: በንግድ ድርጅቶች የሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ያሉ አዝማሚያዎችን እና ድግግሞሾችን በመተንተን የሥርዓት ችግሮችን በመለየት አሠራራቸውን በዚሁ መሠረት ማስተካከል ይችላሉ፤
- ሁለተኛ፣ እነዚህ ስልቶች ቅሬታዎች ከተለዩ በኋላ እንዲፈቱ እና አሉታዊ ተጽዕኖዎች በንግድ ድርጅቱ ቀድሞ እና በቀጥታ እንዲታረሙ በማድረግ ጉዳቶች እንዳይደርሱ በመከላከል እና ቅሬታዎች እንዳይባባሱ ያደርጋሉ::

እንደነዚህ ያሉ ስልቶች አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ማንኛውንም ትክክለኛ ሥጋቶች ለመለየት በተለየ ያለመ እንጂ አቤቱታው ወይም ቅሬታው ለመቅረብ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መፈጸም ቅድመ ሁኔታ አይደለም:: እነዚህ ሥጋቶች ተለይተው ካልተፈቱ፣ ከጊዜ በኋላ ወደ ከፍተኛ አለመግባባቶች እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሊሸጋገሩ ይችላሉ::

የአሠራር ደረጃ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች በተግባር ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የተወሰኑ መስፈርቶችን የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው (መርሕ 31):: እነዚህ መስፈርቶች እንደ ልኬት፣ ግብአት፣ ዘርፍ፣ ባህል እና ሌሎች መመዘኛዎች ፍላጎት መሠረት በተለያዩ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች ሊሟሉ ይችላሉ::

የአሠራር ደረጃ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች ለባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና የጋራ ድርድር ሂደቶች ጠቃሚ ማሟያዎች ሊሆኑ የሚችሉ ቢሆንም ሁለቱንም መተካት አይችሉም። እነዚህ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች ከሠራተኛ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሕጋዊ የሠራተኛ ማኅበራትን ሚና ለማዳከምም ሆነ፤ የፍርድ ቤት እና ሌሎች ከፍርድ ቤት ውጪ ያሉ የቅሬታ መፍቻ ስልቶችን ለመከልከል ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።

**30. ከሰብአዊ መብቶች ጋር የተገናኙ ደረጃዎችን በማክበር ላይ የተመሠረቱ ኢንዱስትሪዎች፣ ባለብዙ ባለድርሻ አካላት እና ሌሎች የትብብር ጅምሮች ውጤታማ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።**

***ማብራሪያ***

ከሰብአዊ መብቶች ጋር የተገናኙ ደረጃዎች በኢንዱስትሪ አካላት፣ ባለ ብዙ ባለድርሻ አካላት እና ሌሎች የትብብር ተነሳሽነቶች በሥነ ምግባር ደንቦች፣ በአፈጻጸም ደረጃዎች፣ በሠራተኛ ማኅበራት እና በተሻጋሪ ኮርፖሬሽኖች መካከል በሚደረጉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ተመሳሳይ ሥራዎች በሚደረጉ ቃል ኪዳኖች ከጊዜ ወደ ጊዜ መንጸባረቅ እየጨመረ መጥቷል።

እንደዚህ ዓይነት የትብብር ተነሳሽነቶች የተጎዱ ወገኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በሚመለከተው ቃል ኪዳን የተገቡ ኀላፊነቶች አልተሟሉም ብለው በሚያምኑበት ጊዜ ሥጋቶቻቸውን ሊያነሱ የሚችሉበት ውጤታማ የቅሬታ ማቅረቢያ ስልቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። እንደዚህ ዓይነት የቅሬታ ማቅረቢያ ስልቶች ካልተመቻቹ የትብብር ተነሳሽነቶቹ ተቀባይነት አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል። ስልቶቹ በግለሰብ አባላት ደረጃ፣ በትብብር ተነሳሽነት ወይም በሁለቱም ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ስልቶች ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያደርጉ እና አሉታዊ የሰብአዊ መብቶች ተጽዕኖዎችን ለማስተካከል የሚረዱ መሆን አለባቸው።

## ከፍርድ ቤት ውጪ ያሉ የቅሬታ ስልቶች የውጤታማነት መስፈርቶች

**31. *መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ከፍርድ ቤት ውጪ ያሉ የቅሬታ ስልቶችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚከተሉት መሆን አለባቸው፦***

(ሀ) ሕጋዊ፦ እንዲጠቀሙ ከታሰቡ ባለድርሻ አካላት እምነት እንዲኖራቸው ማስቻል እና ለቅሬታ ሂደቶች ፍትሐዊ አሠራር ተጠያቂ መሆን፤

(ለ) ተደራሽ፦ እንዲጠቀሙ የታሰቡ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚታወቁ፣ እና ተደራሽነታቸው ላይ የተለየ መሰናክሎች ሊያጋጥሟቸው ለሚችሉ በቂ እርዳታ መስጠት፤

(ሐ) ተገማች፦ ለእያንዳንዱ ደረጃ አመላካች የጊዜ ገደብ ያለው ግልጽ እና የታወቀ አሠራርን ማቅረብ፣ እና ያሉትን የሂደት እና ውጤት ዓይነቶችን እና የትግበራ ክትትል ዘዴዎችን ግልጽ ማድረግ፤

(መ) ፍትሐዊ፦ በፍትሐዊ፣ በመረጃ የተደገፈ እና በአክብሮት የተሞላ የይገባኛል ጥያቄ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ ምንጮችን፣ ምክሮችን እና ዕውቀቶችን ለማግኘት ቅሬታ ያላቸው አካላት ምክንያታዊ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ መፈለግ፤

(ሠ) ግልጽ፦ ቅሬታ ያቀረቡ አካላት ስለሂደቱ እንዲያውቁ ማድረግ፣ እና በውጤታማነቱ ላይ እምነት ለመፍጠር እና ማንኛውንም የሕዝብ ፍላጎት ለማሟላት ስለ ስልቱ አፈጻጸም በቂ መረጃ መስጠት፤

(ረ) ከመብቶች ጋር የሚጣጣም:- ውጤቶች እና መፍትሔዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከታወቁ የሰብአዊ መብቶች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

(ሰ) ቀጣይነት ያለው ትምህርት ምንጭ:- አሠራሩን ለማሻሻል እና የወደፊት ቅሬታዎችን እና ጉዳቶችን ለመከላከል የሚረዱ ትምህርቶችን ለመለየት አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ፤

የአሠራር ደረጃ ስልቶች ደግሞ እንደሚከተለው መሆን አለባቸው፦

(ሸ) በተሳትፎ እና በንግግር ላይ የተመሠረተ:- በንድፍ እና በአፈጻጸማቸው ላይ አጠቃቀማቸው የሚመለከታቸውን የባለድርሻ አካላትን ማማከር፣ እና ቅሬታዎችን ለመፍታት እንደ መፍትሔ በውይይት ላይ ማተኮር፤

*ማብራሪያ*

የቅሬታ መፍቻ ስልት ዓላማውን ሊያሳካ የሚችለው ሊገለገሉበት የታሰቡት ሰዎች ስልቱን ካወቁት፣ ካመኑበት እና ሊጠቀሙበት ከቻሉ ብቻ ነው:: እነዚህ መመዘኛዎች ከፍርድ ቤት ውጪ ያለ የቅሬታ መፍቻ ስልት ለመንደፍ፣ ለመከለስ ወይም ለመገምገም መለኪያ በመሆን በተግባር ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ይጠቅማሉ:: በደንብ ያልተነደፉ ወይም በደንብ ያልተተገበሩ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች የተጎዱ ባለድርሻ አካላት በሂደቱ ውስጥ ያላቸውን

ዐቅም ማጣት እና አለመከበር ስሜት በማባባስ በመካከላቸው ያለውን ቅሬታ ሊያባብሱ ይችላሉ።

የመጀመሪያዎቹ ሰባት መመዘኛዎች በማንኛውም መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ፣ በክርክር ወይም በውይይት ላይ የተመሠረቱ የቅሬታ መፍቻ ስልቶችን ይመለከታሉ። ስምንተኛው መመዘኛ ደግሞ የንግድ ድርጅቶች ለሚያስተዳድሯቸው የአሠራር ደረጃ የቅሬታ መፍቻ ስልቶች የተለየ ነው።

“የቅሬታ መፍቻ ስልት” የሚለው ቃል እዚህ ላይ እንደ የሥነ ጥበብ ቃል ነው። ለተወሰነ ስልት ሲተገበር ቃሉ ሁል ጊዜ ተገቢ ወይም አጋዥ ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን የውጤታማነት መስፈርቶቹ ለሁሉም አንድ ዓይነት ናቸው። በተወሰኑት መስፈርቶች ላይ አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

(ሀ) ባለድርሻ አካላት እንዲጠቀሙ የታሰበን አንድ ስልት ለመጠቀም ከመረጡ ስልቱን ማመን አለባቸው። ባለድርሻ አካላት በስልቱ ላይ ያላቸውን እምነት ለመገንባት አንዱ አስፈላጊ ምክንያት በቅሬታ መፍቻ ሂደቱ ውስጥ የሚሳተፉ ወገኖች በሂደቱ ፍትሐዊ ትግበራ ላይ ጣልቃ እንዳይገቡ የማረጋገጥ ኀላፊነት መኖር ነው።

(ለ) የስልቱ ተደራሽነት እንቅፋቶች ስለ ስልቱ ግንዛቤ ማነስ፣ ቋንቋ፣ ማንበብና መጻፍ፣ ወጪዎች፣ አካላዊ መገኛ እና የበቀል ፍርሃትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

(ሐ) አንድ ስልት እንዲታመን እና ጥቅም ላይ እንዲውል ስልቱ ስለሚያቀርበው አሠራር ይፋዊ መረጃ መስጠት አለበት። አንዳንድ ጊዜ ተለዋዋጭነት አስፈላጊ ሲሆን ካልሆነ በስተቀር ለእያንዳንዱ የሂደት ደረጃ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ በተቻለ መጠን መከበር አለበት፤

(መ) በንግድ ድርጅቶች እና በተጎጂ ባለድርሻ አካላት መካከል በሚፈጠሩ ቅሬታዎች ወይም አለመግባባቶች፣ ተጎጂ ባለድርሻ አካላት ብዙ ጊዜ መረጃ እና ባለሙያ የማግኘት እድላቸው በጣም አናሳ ሲሆን፣ እነዚህን ለማግኘትም የሚያስችል ገንዘብም ብዙ ጊዜ ይጎድላቸዋል። ይህ አለመመጣጠን ካልተስተካከለ፣ የፍትሐዊ ሂደትን ስኬት እና ግንዛቤን ሊቀንስ ከመቻሉ በተጨማሪ ዘላቂ መፍትሔዎችን ለማምጣት አስቸጋሪ ያደርገዋል፤

(ሠ) ስለ የግል ቅሬታዎች ሂደት፣ በሂደቱ ውስጥ ለሚሳተፉ ወገኖች ጋር በመደበኛነት መነጋገር በሂደቱ ላይ ያላቸውን እምነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። የስልቱን አፈጻጸም ለሰፊ ባለድርሻ አካላት በስታቲስቲክስ፣ በጉዳይ ጥናቶች ወይም ስለ አንዳንድ ጉዳዮች አያያዝ

በበለጠ ዝርዝር መረጃ ግልጽ ማድረግ የስልቱን ተቀባይነት ለማሳየት እና በስልቱ ላይ ያለን ሰፊ እምነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በቅሬታ መፍቻ ሂደቱ ውስጥ በሚሳተፉ ወገኖች መካከል የሚደረግ ውይይት እና የግለሰቦች ማንነት ምስጢራዊነት የተጠበቀ እንደሚሆን ማረጋገጫ መስጠት አለበት፤

(ረ) ቅሬታዎች ብዙውን ጊዜ ከሰብአዊ መብቶች አንፃር የማይቀረጹ ሲሆን ብዙዎች በመጀመሪያ የሰብአዊ መብት ሥጋቶችን አያነሱም። ይህ ቢሆንም ውጤቶች በሰብአዊ መብቶች ላይ አንድምታ በሚኖራቸው ጊዜ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ካላቸው ሰብአዊ መብቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፤

(ሰ) የቅሬታ ድግግሞሽን፣ ዘይቤዎችን እና መንስኤዎችን በመደበኛነት መመርመር ስልቱን የሚያስተዳድረው ተቋም ለወደፊቱ ጉዳት እንዳይደርስ ሊቀየሩ የሚገባቸው ፖሊሲዎችን፣ ሂደቶችን ወይም ልምዶችን እንዲለይ እና ተጽዕኖ እንዲያሳድር ያስችለዋል፤

(ሸ) የአሠራር ደረጃ የቅሬታ መፍቻ ስልት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ቡድኖች ጋር ስለ ንድፉ እና አፈጻጸሙ መወያየት ፍላጎታቸውን እንደሚያሟላ፣ በተግባር እንደሚጠቀሙበት እና ስኬታማነቱን ለማረጋገጥ የጋራ ፍላጎት እንዲኖር ያስችላል። አንድ የንግድ ድርጅት በተመሳሳይ ሰዓት ቅሬታዎች የሚቀርቡበት እና የቅሬታዎችን ውጤት በራሱ መወሰን ከተቀባይነት አንጻር ስለማይችል፣ እነዚህን ዘዴዎች በውይይት ስምምነት ላይ የተደረሱ መፍትሔዎች ላይ ማተኮር አለባቸው። ክርክር በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ ይህ ሕጋዊ እና ገለልተኛ ወደሆነ የሦስተኛ ወገን ስልት መቅረብ አለበት።

የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

www.ehrc.org
**ስልክ**:- +251-11550 4031
**ኢሜል** :- info@ehrc.org